ውም ። ከባድ ዝምታ ዋጠው ።…

ከዚያ ጊዜ በኋላ በአለቆቹ የቂምና የጥርጣሬ መነፅር ውስጥ ገባ ። ያዘዙትን ይፈፅማል ። ያልተደረገውን እንደተደረገ አድርጎ እንዲፅፍ ይታዘዛል ። ቢያምንበት ባያምንበት መፈፀም ግዴታው ነበር ።

ከስራ ባልደረቦቹ ውስጥ ደግሞ ተጠላፊዎቹና ጠላፊዎቹ በዝተዋል ። እሱ ከተጠላፊዎቹ ነው ። የራሱንም ሆነ ጠቅላላ ተጠላፊ ጋዜጠኞች ሁኔታን ሲያስተውል "ጋዜጠኛነት ወሬ ኮማሪነት ፣ ጋዜጠኛ ወሬ ኮማሪ!" ማለት ጀመረ ፣ ከራሱ ጋር ሲወያይ ።

ጠልፎ በመጣል በኩል ደግሞ ግራ ኮሌታው ላይ የሌኒንን ምስል የሚለጥፈው አንድ አይናው አምደ ማርያምን የሚያክል ማንም አልነበረም ፤ በብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ህንፃ ውስጥ ።

አምደ ማርያም አንዳንድ ጊዜ 'የቃላት ትራፊክ!" እየተባለ ይጠራ ነበር ። ታዲያ ፊቱ አይደለም ። የሚተማመኑ ተሰባስበው እንደዋዛ ሲያወሩ ነው ። ቃላትን ከቃላት እያዋጋ ብዙዎችን ለችግር የዳረገ ነው ይባላል   በሌለበት ። በ69 አመተ ምህረት አካባቢም በሌኒን ስም ይምል እንደነበር ይነገራል ።

አንድ በሞንም አምደ ማርያም የድንቃለም አለቃ ሆኖ ነበር ። በዚህ የስራ ዝምድናቸው ምክንያት ድንቃለም ያዘጋጀው  ፅሁፍ እንዲፀድቅለትና ወደ ህትመት እንዲላክ ለአምደማርያም ያቀርባል ።

"ኢትዮጵያ ስትል ምን ማለትህ ነው?" ይለዋል አምደ



ማርያም ፤ አንድ ቀን ።

"ኢትዮጵያ ስል ያው የምናውቃት ኢትዮጵያን ማለቴ ነዋ!" ድንቃለም በአጭር ይመልሳል ፤ የአምደ ማርያም አመጣጥ እየገባው ።

"አባባሌን ግልፅ ላድርግልህ! ኢትዮጵያ ስትል የትኛዋን ኢትዮጵያ ማለትህ ነው ? አሻሚ ነገር'ኮ ሆነ ። እኛ ጋዜጠኞች ነገሮችን ግልጥልጥ አድርገን ፤ ሀቅን አፍረጥርጠን መፃፍ አለብን ። የጋዜጠኛ መዝገበ ቃላት ፀጣም ትልቅ ነው ። የጋዜጠኛ ዋና ካፒታሉ ቃላት ናቸውና!…"

"ኢትዮጵያ ስል ይቺ ኢትዮጵያ ማለቴ ነው" ብሎ በንዴት ወለሉን በጫማው መታ መታ አደረገና "ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ሌላ አገር ስለሌለ ለምን አሻሚ ይሆናል?" አለው ።

"አልገባህም ! የምልህን በፖለቲካ አይን ብታየው ። ሌኒን ሁሉን ነገር በፖለቲካ አይን ማየት ይወድ ነበር ይባላል።" ከንፈሩን መጠጠ ። ቀጠለና "ለምሳሌ ውሀን እንውሰድ ። እኛ የምንጠጣውን ውሀና ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሚጠጡትን ውሀ በእኩል አይን ትመዝነዋለህ?" በሀሳቡ ያሸነፈ ይመስል የዛጉ ጥርሶቹን እያሳየው ሁለት እጆቹን ዘረጋለት ። "አቶ ድንቃለም! ኢትዮጵያ አንዲት ብትሆንም ብዙ ናት!"

"አልገባኝም!"

"አትቸኩል፤ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም። አፄዎቹ ኢትዮጵያ ፣ የፊውዳሎች ኢትዮጵያ ፣ የወያኔ ግንጥልጥል ኢትዮጵያ ፣… መልኳ ብዙ ብዙ ነው ። እና ግልፅ ይደረግ!

በተለይ ደግሞ እኛ ‘አዲሲቷ ኢትዮጵያ’ የምንላት ሳታጣ ያጣች ፤ አንጡራ ሀብቷን በጀግኖች ልጆቿ ደምና አጥንት ክፋይ ጠብቃ የኖረች ፤ ኩሩ አፍሪካዊት እመቤት እንደመሆኗ በለቧ ስትፅፍ መነፅርህን ከዚያ አንፃር ብታስተካክለው ጥሩ ነው ።”

“እንዳልከው በርግጥ ሀቀኛ ጋዜጠኞች አይቸኩሉም ። አይክለፈለፉም ። የእውነት ጠበቆችም ናቸው ። ማንንም ለማወደስ ሲሉ በቃላት አይጫወቱም” አለና በአሽሙር ጀመረ ፤ ድንቃለም ። ቀጠለና “የማውቃት አንዲት ኢትዮጵያ ናት ። ያልከኝን ሁሉ የምፅፍ ራሳ'ር ፀሀፊሀ አይደለሁም” አለ ፍርጥም ብሎ ።

“ጋዜጠኛ አይናደድም ። ጋዜጠኛ በሂስ ያምናል ። ጋዜጠኛ ስህተቱን ፈጥኖ ያርማል ። ጋዜጠኛ አለቃውን ያከብራል ።”

“ግን አሻንጉሊት አይደለም!” ድንቃለም አቋረጠው ።

“ማን አሻንጉሊት አደረገው?” አምዶ ማርያም አፈጠጠ ። ድንቃለም አልመለሰለትም ።

“የታዘዝከውን እንድትሰራ የሚያደርግህ አመራሩ ነው። አመራሩ ደግሞ የአገሪቱ ነው ። ‘ጋዜጠኛ አሻንጉሊት አይደለም!’ ስትል አሻንጉሊት ያደረገው’ አለ ማለትህ ነው። ይህ ለበላይ አካል የሚቀርብ ጉዳይ ነው ። ግን ባልረባ ክርክር አስር ደቂቃ አጠፋን ። አብዮቱን በአስር ደቂቃ እንደጐተት ነው ይገባሃል?”

ክስ በዛበት ፤ ከቃላት እያጋጩ ፤ ቃላትን እየበለቱ ሰላም ነፈጉት ። እፎይታ አጣ ። ፍርሀትና ስጋት ተጫጫኑት ።



ችሎታውን ሊጠቀሙበት በለፈለጉ ግን አላባረሩትም። አላሰሩትም ። ግን ያስጨንቁታል ። እድገት ይከለክሉታል ። የሚቀመጥበትን ወንበርና የሚውልበትን ቢሮ እንኳ መጠራጠር ጀመረ ። አንድ ፅሁፍ ፅፎ ሲጨርስ ቢያንስ አስር ጊዜ ያነበዋል ። እና ሙያውን ጠላው ።

“ጋሼ አንድ ነገር ልጠይቃዎት ብዬ ነበር!” ተቅለሰለሰችበት ፤ ባለ ጥቁር ጠላዋ ።

“ምን ነበር ጥያቄሽ?”

“የማውቀዎት መስሎኛል!”

“ታዲያ ምን አለ!? ግን የት ቦታ ነው የምታውቂኝ?” ጠርሙሱን አንስቶ ቀዳና ብርጭቆዋን በአንድ ትንፋሽ ከለበሳት ።

“እንጃ!… ብቻ አንድ ቦታ…” ብላ ማሰብ ቀጠለች ።

አንድ ቦታ ላይ የሚተዋወቁኝ ሰዎች በሚሊዮን ይቆጠራሉ ። ግን እውቂያ አይባልም ። ሌላ ጠርሙስ አምጭልኝ!”

ከመደርደሪያው አንድ ጥቁር ጠላ የሞላ ጠርሙስ አውርዳ ፊት ለፊቱ ጉብ አደረገችለት ።

“አሁን አስታወስኩት ጋሼ…አስታወስኩት!” እያጨበጨበች ።

“በይ እስኪ አምጭው!” አላት እያፋሸገና “ከኔ ጋር አድረሃል”

“ብርሃንና ሰላም ህንፃ ውስጥ ነው ። አንድ ጊዜ መጥቼ ነበር። እኒያ የናንተ ጓደኛ…ጉድጓድ ይከተታቸውና አንድ ወር ሙሉ ጥቁር ጠላየን በዱቤ ሲጠጡ ከርመው ሂሳብ ላይ ነገ ዛሬ እያሉ ሲያጉላሉኝ ከስሻቸው ፤ መጥሪያ ልሰጣቸው ቢሮአ

ቸው ድረስ ስመጣ አግኝቸዎታለሁ ። እንዳውም በሽምግልና ገብተው ነበር ። ያውም እንኳ እዳቸውን ራስዎ ነበር የከፈሉላቸው ። ስድሳ ሁለት ብር ከኪስዎ መዘው አልሰጡኝም? እንዴት ረሱት?"

"አሁን ገና ትዝ አለኝ! አምስት አመት ሊሆነው አይደል?" ክብሪት ጭሮ ሲጋራውን ካቀጣጠለ በኋላ "ለምን ከሰስሽው ግን? በዚያን ወቅት ከባድ ችግር ስለነበረበት ነው እንጂ አያስቀርብሽም ነበር ። ጨዋ ሰው ነው ። ጥቂት ብታተገሺው ደግ ነበር" አላት አበራን እያስታወሰ ። መጥሪያ ይዛ ስትመጣበት ምን ያህል እንዳፈረና "መጣች! መጣች! የለም በላት!...እያለ ቁም ሳጥን ውስጥ ለመግባት ያደረገው ጥድፊያ ትዝ አለው ።

"ምን ማለትዎ ነው ጋሼ? ታዲያ ምን ላድርግ? ከኔ እሳቸው ይሻላሉ ። የወር ገቢ እንኳ አላቸው ። ከጠላ ከሚገኝ ገቢ ተብሶ ባዶዬን አጨብጭቤ ልቅር? ስድሳ ሁለት ብር'! ነው ። ሶስት መቶ ጠርሙስ ጠላ ሸጬ የማገኘው ትርፍ ነው ። እንዲያውም ለምን ላዋርዳትው ብዩ ነው እንጂ ብዙ እዳ ነበረባቸው ። ግን ምን ያደርጋል?"

"ሌላ ምን የሚሉት እዳ ነበረበት?" በመገረም ተመለከታት ።

"ኧረ ይቅር! ምኑ ይወራል!"

"ካልተወራ ይቅር!" ትከሻውን ከፍ አደረገ ።

"ምን መሰለዎት? ብቻ ያሳፍራል!...ግን ምኑ ያሳፍራል? ለምደውኝ ነበር" አለችና ተሽኮረመመች ።

"መላመድ እዳ ነው እንዴ?"



"ይቀልዳሉ መሰለኝ? አሁን ማን ይሙት ነገሬ ሳይገባዎት ቀርቶ ነው? አንድ ወር ሙሉ ለደመወዝ እያሉ እኔ ጋር አድረዋል ። ..." ሀፍረት የተሰማት ይመስል አቀረቀረች ።

"በስመ አብ በይ! ባለትዳር ነው' ኮ? እንዴት እንዲህ ትያለሽ?"

"ተባለ እንዴ? ጋዜጠኞች ስትባሉ ቀልድ ትወዳላችሁ። አሁን ሊያናግሩኝ ነው እኮ! ስንቱን እናውቀዋለን... ባለትዳርም ይሁን ወንደላጤ ሁሉንም በአይነት በአይነቱ አይተናል ። ሙች ይታወቅባቸውና? ኧረ ባለትዳሩ ይብሳል!"

"እድለኞች ናችኋ ታዲያ!" አለ ።

"በልተን ማደራችን ነው?"

"እሱን ያልታደለ ስንት አለ!"

"እንስሳ እንኳ በልቶ የድራል ። በልቶ ማደር ካልቻለ ለምን ይኖራል? ራሱን ማጥፋት አለበት ። ምን ሊያገኝ ብሎ ይኖራል? ምንን ተስፋ አድርጎ ይጠባበቃል? በአስር ሳንቲም ገመድ ህይወቱን ለምን ሲጥ አያደርጋትም? ስለኛ የሚያስብ'ኮ ማንም የለም ። ስንቱን ቻለን መሰለዎት?"

"ልክ ነሽ! ሴቶች ጭቆና አለባችሁ ። ግንኙነት ስታደርጉ እንኳ ሁል ጊዜ ከታች ነው የምትሆኑት ።"

አንድ ወጣት ድንገት ከፍሏ ውስጥ ጥልቅ አለና ያለምንም ሙዚቃ ስብርብር ፣ ዝልፍልፍ ማለት ጀመረ ።

"ሙዚቃ ! ሙዚቃ!" ብሎ ጮኸ ወጣቱ ።

"መጀመሪያ ምን ልታዘዝ?" አለችው ኮስተር ብላ ።

"እንቺን!" አሁንም ይብረከረካል ።

"ከኔ በፊት?" —

"ጠላ!" አላትና ባንኮኒዋን ተደግፎ ቆመ ። ግንባሩ ላይ ላብ ቸፍፍ ብሏል ። የተቀዳለትን ብርጭቆ ጠላ በአንድ ትንፋሽ አጋባና እጇን ይዞ እየጐተተ ወደ ጓዳ ገባ ። ጥቂት ካንሾካሾኩ በኋላ መጋረጃውን ሰብሰብ አድርጋ አንገቷን ብቅ አደረገችና "ጋሼ ቤቱን ይጠብቁልኝ ። አሁን መጣሁ ። አደራ!" አለችው ።

"እንዴ! ነይ ውሰጂ ሂሳብሽን!" ጮኸባት ድንቃለም የውስጥ ኪሱን እየዳበሰ ።

"ታዲያ ምን አስቆጣህ?"

የአራት ጠርሙስ ጥቁር ጠላ አራት ብር ጣለላትና ውልቅ አለ ።

"ምን ይጨማለቃል" አለችው በሩ ላይ ብቅ ብላ ። ወዲያው በሯን ዘጋች ። ድንቃለም የወሲብ ስሜቱ ተቀስቅሶበት ፣ በገጠመው ድርጊትም እየተበሳጨ ወደ ወይዘሮ ባፈሳ ቤት አዘገመ ። ኪሱ ውስጥ ድፍን ሀምሳ ብር ቀርቶታል ። ሰአቱን ሲመለከት አምስት ሰአት ይላል ፣ ከምሽቱ ።

"ባፌ! ቢራ አለሽ?" አለ ገና ከመግባቱ ።

"ድንቄ! ግባ...ቅድም'ኮ ተበሳጭቼ ስለነበር ነው ። አንድ ጉረኛ አበሳጨኝ ። የተማረ ይግደለኝ ። በተለይ ጋዜጠኛ ! አይ አንደበት ...አይ ለዛ...አይ ጨዋታ...የጋዜጠኛ ሚስት ታደለች! ...ሳትስቅ የምትውልበት ቀን ይኖር ይሆን?" ሁለት ጠርሙስ ቢራ ከፍተው አንዱን ለድንቃለም አቀረቡለት ፣ ለራሳቸውም አንድ ጨበጡ ። ደጋገሙ ። የተቀመጡት ጐን ለጐን ስለነበር ሳብ አድርጎ አቀፋቸው ።

"ልዝጋው እንዴ በሩን?"



"አዳሬ እዚሁ ነው!" አለ ።

"ይሻላል ብለህ ነው?"

"ምነው ባፌ? ምርጫው ያንቺ ነው!"

"እስቲ እናየዋለን!" ወይዘሮ ባፈሳ አቅማሙ ። ልቡን ሊሰቅሉት ፈልገዋል ። 'ወንድ ልጅን ምንጊዜም አይለምዱትም' የሚል አባባል አላቸው ። ከድንቃለም የበለጠ የሚጋብዝ ፣ ገንዘቡን ከምንም ሳይቆጥር ከኪሱ እያወጣ የሚረጭ ከመጣ አይናቸውን ሳያሹ ይቀይሩታል ።

"ይኸው የናንተ ጋዜጣ በጨረታው አይገደድም ነው የሚለው?" አሉና ሳቁ ።

"አዎ ባፌ! ማንኛውም ነገር በጨረታው አይገደድም!"

አንድ ጠቆር ያለ ፣ ቦርጫም ሰውዬ ኮረጀውን አንጠልጥሎ ዘው አለ ። ፊቱ ተኮሳትሯል ። ግልምጫው ከሚጉረጠረጡት አይኖቹ ጋር ሲታይ ከሞቀ አምባ ጓሮ አምልጦ የመጣ ያስመስለዋል ።

"ቢራ! ቢራ!" አለና በወይዘሮ ባፈሳ ላይ ተኮሳተረ ።

"ሀሩይ ሙት! ዛሬ እንዴት ይሙቅ ቤቱ? ስትቀርብኝ ጊዜ ጭንቅ አለኝ ። ቢራ እጠጣለሁ" አሉት የውሸት ሳቃቸውን እያፈኑ ።

"ጠጭ! ማን ከልክሎሽ! እኔ ሀሩይ ቢራ እንጂ ወሬ አልጋብዝም!" አለና በድንቃለም ላይ አፈጠጠ ። ኮረጆውን ከፍቶ 'የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ' ጋዜጣ አወጣ ።

"ዛሬ የወጣ ነው እንዴ?" ድንቃለም ነበር ።

መልስ አላገኘም ።

"አንድ ጊዜ ታውሰኛለህ? ይቅርታ ግን..."

"ምን ያደርግልሀል? የፃፍከው ራስህ ፤ ያዘጋጀኸው ራስህ ፡ ለምን ሳንበው ትለኛለህ? አዲስ ነገር የለውም ። የውሸትና የውኸንብር ሚስቶ ነው!" ሀሩይ የቢራ ጠርሙሱን አነሳ ። ቦርጬን አሻሸና ከለበሳት ።

"የውሸትና የውኸንብር ሚስቶ ስትል ምን ለማለት ፈልገህ ነው?"

"አርፈህ ጠጣ! ማን አናገረህ አሁን? ህግ ሳስከብር እንጂ ወሬ ስቃርም አልዋልኩም ። ልረፍበት!" አለና ሀሩይ ጋዜጣውን አጣጥፎ የኰረጀው የውጭ ኪስ ውስጥ ከተተው።

"ወሬ የሚቃርም ማነው?"

"ወሬኛ ነዋ!"

"ወሬኛው ማነው?" ድንቃለም ቱግ አለ ።

"አጥብቆ ጠያቂ የእናት ሞት ይረዳል !' አሉ" ሀሩይ ፈገግ አለና "ጋዜጠኛ ነዋ! ጠበቃ መሰለህ? የወሬ ቋት!..."

ድንቃለም አላስጨረሰውም ። "የት ታውቀኛለህ? እብድ ነህ?" አለው ሲጋራውን ሊለኩስ ክብሪት እየጫረ ።

"የወሬ ቋት ! ይልቅ ጠጣ! ከኋላህ መጥቼ ሶስት መጠጣቴ ነው ። አንተ ጡጦ የሚጠባ ህፃን ይመስል አንዷን ለመጨረስ ታቃትታለህ!"

ወይዘሮ ባፈሳና ጠበቃው ሀሩይ አንድ ላይ ሳቁ ። ድንቃለም ሲጋራ ለኮሰ ።

ጠበቃው ከፍተኛ ቅናት ስለሚሰማው ወይዘሮ ባፈሳ ቤት ሲጠጣ ያገኘውን ሁሉ ይገላምጣል ። በነገር ዱላ



ይወግራል ። ድንቃለምን ያውቀዋል ፣ ከወይዘሮ ባፈሳ ቤት ወጣ ሲል በእግሩ እንደሚተካ ።

ጠበቃው ሀሩይ ያን እለት አዳሩን ከወይዘሮ ባፈሳ ጋር ለማድረግ ወስኖ የመጣ ነበር ። እቅዱ እንዳይሰናከልበት ድንቃለምን ለማባረር ከወዲሁ ነገር ጀምሯል ።

"ተጫወቱ እንጂ! የምን ዝም ዝም ነው?" ብለው ወይዘሮ ባፈሳ በሁለቱም ላይ አፈጠጡ ።

"ቢራየ አለቀች!" አሉ በዘፈን ቅላፄ ። ጠርሙሷን አንስተው ወደ አይኖቻቸው አስጠግተው ተመለከቷት ።

"ጋዜጠኛው አይጋብዝሽም ማለት ነው?" ጠበቃው ሀሩይ ነበር ።

"ድንቄ!" ድንቃለምን የጎሪጥ ተመለከቱት ፣ ቀይ ዳማ ፊታቸውን በሚያግባባ ፈገግታ እየቃኙ ።

"ጠጪ!" አለ ድንቃለም በታከተ አነጋገር።

"ታድዬ!" አሉና ወይዘሮ ባፈሳ እየተገናደሱ ወደ ጓዳ ገቡ ።

"አንድ ቢራ ብቻ ነው?" ጠበቃው ሀሩይ ድንቃለምን እየተመለከተ ሳቀበት ።

ወይዘሮ ባፈሳን ጨምሮ ጋዜጠኛውና ጠበቃው ተፋጠዋል ። በመካከላቸው ከባድ ዝምታ ሰፍኗል ። ጠበቃው ፣ ጋዜጠኛው ድንቃለምን የሚያስወግድበት መንገድ ያሰላስላል ። ጋዜጠኛው ደግሞ የአዳሩ ጉዳይ ብዙም ሳያሳስበው ስለሙያው ፣ ስለስራው ፣ ስለኑሮው...ያስባል ፤ ይጨነቃል ፤ ይሰጋል ። አደጋ እየታሰበው ተጠቧል ።

ወይዘሮ ባፈሳም ያስባሉ ። ይኸው ፍጥጫ የት እንደሚ

ደርስ አስግቷቸዋል ። ከጋዜጠኛውና ከጠበቃው አንዱን
ማስወጣታቸው የማይቀር ነው ። ከተቻለ አንዱን ይሸንግሉ
ታል ፤ የተለያየ ዘዴ ፈጥረው ። ሽምግልናውና ማግባባቱ
ካልሰራ "በህግ አምላክ!" ብለው እሪታቸውን ሊለቁት
አቅደዋል ።

ማንን እንደሚያስወጡ ግን ጨንቋቸዋል ። ጋዜጠኛው
ድንቃለም ጥሩ ተጫዋች ነው ። አንደበቱ ይጣፍጣቸዋል ።
በፍቅር ጨዋታ ያረካቸዋል ። ግን በቂ ገንዘብ የለውም ። በቂ
ገንዘብ ስለሌለው ደግሞ ሊያርቁት አይፈልጉም ። በመልክ
መልካምነቱ ከጠበቃው ይመርጡታል ። ረዘም ያለ ቁመና
ውና ቅላቱ ፤ ጎላ ያሉት አይኖቹና ሉጫ ፀጉሩ ማርኳቸዋል ።

ጠበቃው ሀሩይ ደግሞ በመልኩም ሆነ በፍቅር ጨዋ
ታው ከቁጥር የሚገባላቸው አይነት አይደለም ። በጣም
ይደክምባቸዋል ። ጐኑ አልጋ በነካ በጥቂት ደቃቂዎች ውስጥ
ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይወስደዋል ። በዚህ ስንፍናው ጁንቁ
ታል ። ቢሆንም ግን የማይነጥፍ ገንዘብ አለው ። ግብዣው
የሚያኮራቸው ነው ። አያፍሩበትም ።

ብዙ ካሰላሰሉ በኋላ የገንዘብ ጉዳይ ላይ ልባቸው
አልቆርጥ አለና ጋዜጠኛው ድንቃለምን ለመሸኘት ወሰኑ።

"ምን ልበለው? አዎ! 'ሀሩይኮ ለጋብቻ ፈርሞልኛል ።
ሚስቱ ማለት ነኝ ። ስለዚህ ዛሬ ቤትህ ግባ! ሌላ ጊዜ
አስደስትሀለሁ' ብለውስ? እምቢ ቢል ግን በጥበቃ ጓደ
አስይዘዋለሁ ። በቃ!" እያሉ ፀሀሳባቸው ዘዴአቸውን ሁሉ
አውጠንጥነው እንዳበቁ ድንቃለምን ሊጠሩት ከመቀመጫ



ቻው ሲነሱ ሌላ ሰው ዘው አለ ።
ባፌ! ለኔም ቢራ...ለአንቺም ቢራ!" አለ በጉርናና
ድምፅ ፤ ገና ደጃፉን እንደተራመደ ። የአራት ኪሎው ደላላ
ቾምቤ ነበር ።

ቾምቤ የታወቀ ደላላ ነው ። ታዋቂነቱ በድላላ ብቻ
አልነበረም ። ጉልቤም ነው ። ቾምቤን ማን ደፍሮ ይናገረ
ዋል! ማጅራት መቺም ነው ይባላል ።

ቾምቤ የወይዘሮ ባፌሳ የኖረ ውሽማ ነው ። የኪራይ
ቤት ፤ የሚሸጥ መኪና ፤ ቪዲዮ ፤ ቴሌቪዥን ሲደልል ውሎ
ማታ ወደ ወይዘሮ ባፌሳ ቤት ብቅ ይላል ። የሚጠጣው ቢራ
ነው ። ከቢራ ውጭ ሌላ አይቀምስም ። በቀናው ሰሞን
የወይዘሮ ባፌሳ ጓዳ ቀንና ማታ ክፍት ይሆንለታል ። ደባል
ይመስል ውሎውም አዳሩም ከዚያው ነው ። መኝታ ካግረ
"ሞት የሸተተው አለ? ሞትን ከቾምቤ በነፃ ማግኘት ይቻ
ላል!" ይልና ወይዘሮ ባፌሳ ላይ ያፈጠጡትን ጠጭዎች
ይገላምጣል ። ያኔም ሁሉም ሹልክ ሹልክ እያለ ይወጣለታል
፤ ሂሳቡን እየከፈለ ። የቤቱ በር ወዲያው ይዘጋል ፤ ገና
ሳይመሽም ቢሆን ።

"ሞት የሸተተው አለ? በነፃ እጋብዘዋለሁ!" ሲል
ቾምቤ እንደልማዱ ጮኾ ጋዜጠኛው ድንቃለምና ጠበቃ
ሀሩይ ላይ አፈጠጠ ። "ሂሳብ ከፍለውሻል ባፌ? እነዚህ
ትኋኖች!" የጋበዛቸውን ቢራ ጠርሙስ አንቀው በኩራት
የተኮፈሱትን ወይዘሮ ባፌሳን ቃኛቸው ።

"እያየሀቸው አይደል ቾምቤ?"

ድንቃለም ከኮቱ የውስጥ ኪስ ድፍን ሃምሳ

ሲያወጣ ፡ ጠበቃው ሀሩይም ኪሱን ፈትሶ የገንዘብ ቦርሳውን መዘዘ ።

እያንዳንዳቸው መልሳቸውን ከወይዘሮ ባፈሳ ተቀብ ለው አቀርቅረው ሊወጡ ሲሉ "ቶሎ! እኔ ቾምቤ!...እንደ ጌሾ ሳትወቀጪ ሁልሽም ቶሎ ጥፊ!" በማለት ድልህ አይኖቹን አጉረጠረጠባቸው ።

"ባሬ ቢራ ድገሚኝ!" ሲል ተኩራርቶ ቾምቤ መቀመ ጫውን ተደላድሎ ከመያዙ ባፈና በር ላይ የሚቀባበል የመሳሪያ ድምፅ ተሰማ ። ቾምቤና ወይዘሮ ባፈሳ በፍጥነት ወደበሩ ብቅ ሲሉ የአራት ኪሎው 'ጥበቃ ጓድ' ኡስማን መሳሪያውን በጠበቃውና በጋዜጠኛው ላይ ደግኗል ። "እጅ ወደ ላይ!" ተብለው ሁለቱም እጆቻቸውን ሰቅለው ቆመ ዋል ። "ናውጣ…አይንህ ይውጣና!" አለው ኡስማን ቾም ቤን የጎሪጥ እያየው ።

ቾምቤ እስከ ክርኑ የሰቀሰቃቸው እጅጌዎቹን ቁልቁል እየዘረጋ ወጣና ከነድንቃለም ጋር ተቀላቅሎ ቆመ ።

"ቀጠሮዎችሁ ፀረ አብዮት ወረቀት ለመበተን ነው ፡ አይደል? አሁን ስንት ሰአት ነው?" የመሳሪያውን አፈ ሙዝ እያዟዟረ ደነፋባቸው ። ከድንጋጤያቸው የተነሳ የሚሉት አልነበራቸውም ። "እንደናንተ አይነቶቹን ያለምንም ጥያቄ መድፋት ነበር !! ቶሎ በቀጥታ ወደ ቤታችሁ!!"

ሶስቱም ወደየመንገዶቻቸው ገቡ ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኡስማንና ባፈሳ ከርቀት ሰላምታ በቀር ምንም አይነት ግንኙነት አልነበራቸውም ፡ ለክፉ ቀን ፈጥኖ ደራሺ ይሆንል ኛል በሚል እምነት ባፈሳ ያስጠጉት ኡስማን ጥበቃ ጓድ



ከተባለ በኋላ ነበር ።

የወይዘሮ ባፈሳን በር ራሱ ከውስጥ ቀረቀረና ልብሶቹን አወላልቆ የተንጣለለው አልጋቸው ላይ ተጋደመ ፡ ወይዘሮ ባፈሳን በጉጉት እየተጠባበቀ ።

እቅፉ ውስጥ እንደገቡለት "እነዚህን ሰዎች የት ታውቂያቸዋለሽ? አንቺ ወስላታ!" አላቸው ።

"ኧረ እኔ እቴ! …የት አውቃቸውና? ገላገልከኝ ።"

"ተጠንቀቂ! ያሳስቁሻል።"

"እሽ! …" አሉት ልብሳቸውን እያወላለቁ ።

*ለብርሐኑ አክርር (ሀይል የካቲት) ጥሬ 1982 ።

# የእንጀራ ገመድ

"ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ?" እያለ አላፊ አግዳሚውን የሚለክፈው ወፈፌ በአንድ ወቅት አትክልተኛ ነበር ። በሆነ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ከአንድ ዓመት በላይ በቅን መንፈስ ያገለገለ ሲሆን አንድ ቀንም ከሥራው ቀርቶ አያውቅም ። ያረፈደባቸው ቀናት ቢኖሩ እንኳ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ። በየወሩ ያችን ደሞዙን ለመቀበል ካልሆነ በቀርም ወደ ዋናው ህንፃ ፊቱን አዙሮ አያውቅም ። ከሌሎች ሰራተኞችም ጋር የሚያገናኘው አምብዛም ጉዳይ አልነበረውም ። በእረፍት ጊዜው ጨዋታ ሲያምረው ጠጋ የሚላት አንዲት ፅዳት ሰራተኛ ብቻ ነበረች ። ደመቀች ትባላለች ። ከእርሷ ጋር ሲያወራ በአጋጣሚ ሌላ ሰው ደብለቅ ቢል እንኳ ከመቅጽበት ወደዝምታ ይሸጋገርና ራሱን በሀሳብ ባህር ውስጥ ያስጥ ማል ። ችግሩ ከአይናፋርነት የመነጨ አይመስልም ። አንደበተ ርቱዕ ነው ።

ከስራው ከተባረረ መንፈቅ ሳይሞላው ለወፈፌነቱ ተዳርጎ አስደንባሪ ፍጡር ከሆነ ዓመታት አልፈውታል ። ለመባረሩ ምክንያት የሆነበትንም ጉዳይ የሚሰማው አጣ እንጂ ያነሳል ። ሆኖም መታመኑ ቀርቶበት ከልብ አድምጦ ያዘነለት ወይም ያፅናናው አንድም ሰው አላገኘም ።

በአትክልተኝነት ከቆየባቸው አሥራ አራት ወራት የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ብቻ በቀን ሞያተኛነት አስቆጥሮ በአራተኛው ቋሚ ሆነ ። የመጨረሻዎቹን ቀናት ያሳለፈው ግን በምሬት ነበር ። የተቀጠረበትን እለት እየረገመ ። ተላላኪ ይመስል ፣ ያለወትሮው ከፐርሶኔሉና ከሕዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊው ቢሮዎች ወጣ ገባ ማለቱን ያበዛው ያኔ ነው ። ለስንብትም የበቃው ከሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ጋር የፈጠረው አምባጓሮ እንደሆነ ይወሳል ።

የሚያስገርመው አንድ አትክልተኛ መሬት መርገጥ ከሚጠየፍ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ጋር የከረረ ቅራኔ ውስጥ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ነው ። አጋጣሚው ያልተለመደ በመሆኑ ፣ ምክንያት ብሎ የሚያቀርበውን ሀሳብ የሚያዳምጠውም የሚያምነውም ቢያጣ አያስደንቅም ። ሆኖም “ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ?” እያለ ማነብነብ የጀመረው በስንብቱ ዋዜማ ነው ።

ከስንብቱ በኋላ ያ ሰው በአዲስ አበባ ከተማ “ወፈፈው” በሚል መጠሪያ ብቻ ታውቆ ስሙ ተረሳ ። እንሙት ካሴ መባሉን ግን የሚያውቅ ያውቀዋል ። የደብተራ ካሴ ሁነኛ የበኩር ልጅ ፣ ለ ያውም ወንድ እርሱ ብቻ ሲሆን ፣



ተወልዶ ባደገበት በብቸና አውራጃ ፣ በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ፈደል ቆጥሮ ለድቁና በቅቶ ነበር ። ታታሪ ገበሬም ነበር ይባላል ። ዘመኑ ያመጣበት የገበሬ ማህበራት ቱማታ ፣ የሠፈራና የሚሊሺያ ምልመላ ግርግር አስመርሮት በድንገት ወደ አዲስ አበባ ጠፍቶ ከመጣ በኋላ የውኃ ሽታ ሆኖ የቀረ ሰው ነው ።

አድራሻውን አጠያይቆ ከደረሰበት የሩቅ ዘመድ ዘንድ ተጠግቶ የቋጠራትን ጥሪት እስኪጨርስ ኑሮ አልከፋውም ነበር ። ከአንድ ዓመት በኋላ ግን ዘመድ ተብዬውም ሆነ የከተማው አስተናጋጅነት አከተመበት ። የሚላስ የሚቀመስ እስኪያጣ ወጣ ወረደ ። ሽሮ ሜዳ አካባቢ ፣ የአንድ ድርና ማግ ነጋዴ ማቲዎች ፊደል አስቆጣሪ ሆነ ። የመንደሩንም ህፃናት አሰባስቦ በማስተማር ጥቂት ወራት አሳለፈ ። ግን ያች የቁጥቁጥ ገቢው የዓመት ልብሱን ቀርቶ የዕለት ጉርሱን የምትሸፍንለት አልሆነችም ። ቀጥሎም በመርካቶ ፣ ከዚያም በተክለሃይማኖት ፣ በኋላም በሰንጋ ተራ አካባቢዎች በሽቃይነት ተሰማርቶ ሲያገኝ ጠግቦ ፣ ሲያጣ ደግሞ ጦም ማደሩን ተላመደው ።

ከዕለታት አንድ ቀን ፣ በፋሲካ ዋዜማ ፣ በለስ ቀናው ። ገመድ ብጤ አንጠልጥሎ ከአንድ በግ ገበያ ወደሌላ እየተዘዋወረ ሲሸከም ውሎ ምሽት ላይ ከክንፈ በልሁ ጋር እግዜር ያገጣጥመዋል ።

ክንፈ እንደዛሬው ቦርጩ የሚዋልልና ወደ ኋላው የሚለጠጥ ሰው አልነበረም ። እንጀቱ በረሃብ የታጠፈበት ይመስል ፣ የሚራመደው ጉብጦ ነበር ። ግን እንደ ፊኛ

ከተወጠረ የኪስ ቦርሳው አራት ባለሃምሳ ድፍን ብሮች መዝዞ አንዲት ጠቦት ሲገዛ ያየው አንሙት ይህን ግምት የለወጠው ያኔውኑ ነው ። አንከብክቦለት ጠቦቷን እስከመኪናው ለማድ ረስ ዋጋ አልጠየቀውም ። የተከፈለውም ካሰበው በላይ ሆነለት ።

"አርደህ ብልት ማውጣት ትችላለህ ?" አለው ክንፈ ፣ ያሮጌ አፔሉን የኋላ ኮፈን ከፍቶ በጉን ስፍራ እንዳስያዘለት ።

"አዬ ጌታዬ !" ሲል መለሰለት በአጠያየቁ ተገርሞ ። እንዲያ መባሉን እንደ ነውር ቆጥሮታል ።

"እችላለሁ ወይም አልችልም ማለት እንጂ ጥያቄዬ ማብራሪያ አያስፈልገውም" በማለት አንድ ብር ወርውሮለት ዘወር ሲልበት አንሙት አላስቻለውም ።

"ያቆማሁበት ነው ብዬ ነዋ!" አለው በልመና ቅላፄ ።

"በል ግባ" ብሎት የመኪናውን የኋላ በር ከፈተለት ።

ገብቶ ከክንፈ ኋላ ካለው ባዶ ወንበር ጫፍ ላይ ተቀመጠና ሚዛኑን ለመጠበቅ ሲል የክንፈን መቀመጫ በሁለት እጆቹ ተሞረኮዘ ።

"በዚያኛው ጥግ !" አለው በጣቶቹ እየጠቆመው ። "ዘና ብለህ ተቀመጥ ።"

እየተንፏቀቀ ተጠጋና እግሮቹን ዘረጋ ። አቀማመጡ የመጋደም ያህል ነበር ። ክንፈ ዘወር ብሎ እንኳ ሳያየው መኪናውን እያከነፈ ከቤቱ ደርሶ ጡሩምባውን ለቀቀው ።

አንዲት ጉቶ ቢጤ ፈርጣማ ሴት የውጭውን በር ከፍታ አስገባቻቸው ። ከአለባበሷና ከእጅ አነሳሷ የክንፈ ሠራተኛ እንደሆነች አንሙት ገመተ ። በሩ ሲከፈትለት ጣደፍ ብሎ



ወጣና በጉን እየጐተተ ወደ ጓሮ አመራ ።

ሰፊ ግቢ ያለው ዘመናዊ ቤት ነው ። ግን ከመጠን በላይ ጭር አለበት ። ቢላዋዎች ፣ ለመለቃለቂያ የሚሆነውን ውኃና ሌሎች የሚያስፈልጉትንም ነገሮች ወጣ ገባ እያለች የምታቀ ራርብለት ያችው ሠራተኛ ብቻ ነበረች ።

"ይባርኩልኝ በያቸው" አላት ዝግጅቱን እንዳጠ ናቀቀ ።

ክንፈ በመስኮት ብቅ ብሎ "አንተው አትባርከውም ?" አለው ።

"እስላም ልሁን ክርስቲያን ምኔ ታውቆ ?"

"እስላም ሆነ ክርስቲያን ፣ የቀረበለትን ማዕድ እንደየእ ምነቱ ባርኮ እስከ ቀመሰ ፣ ማንስ ቢያርደው ምናለበት ?"

"አበስገበርኩ !" ብሎ አንሙት ሲያማትብ ፣ ክንፈ ከትከት ብሎ ሳቀበት ።

"በል እረድ ።"

"እሺ ። በስመአብ ፣ ወወልድ ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ..."

"ክርስቲያን ነሃ !"

"የቄስ ልጅ ነኝ" አለው አንሙት ፣ ተፍ ተፍ እያለ ። "ዲያቆንም ነበርኩ ።"

"የት ?"

"ጐጃም ።"

"ወደ አዲስ አበባ ምን አመጣህ ?"

"ስራ ፍለጋ ። እድሌ ሆኖ በከንቱ ስማስን ዘንድሮ አራተኛ አመቴ ።"

"ስራ መች ጠፋ ? የጠፋው ሰራተኛ ነው ። አለሁ ብሎ

የሚቀርበው ሁሉ ዳተኛ ወይ ሌባ ሆነ ።”

“አይ ጌታዬ ! ሁሉ መች እንዲያ ሆነና ?!”

“እንዲያ ብሎ አንገቱን ሰብሮ የሚገባው ነው በመጀመሪያ ደሞዙ ቀና የሚል ፤ በሁለተኛው ደሞዙ ደረቱን የሚገለብጥ ፤ በሦስተኛው አሰሪውን የሚገላምጥ ፣ በአራተኛው ከቀበሌ እስከ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚያሯሩጥ ፤ …”

“እኔ እንዲያ ያለሁ ሰው አይደለሁም” ብሎ አንሙት ቀና ቢል ክንፈ የለም ። ወደ ተግባሩ ተመልሶ ቀና ደፋ ሲል የቤት ሰራተኛዋ ብቅ አለች ፣ ልታግዘው ።

“የምጠጣው ውኃ !” አላት ። ላቡ በግምባሩ ይንቆረቆራል ።

ወደ ቤት ገባ ብላ ማንቆርቆሪያና ብርጭቆ ይዛለት ተመለሰች ። የሞላችለትን በአንድ ትንፋሽ ገልብጦ ቁና ቁና እየተነፈሰ ብርጭቆውን ሲመልስላት “ልድገምህ ?” አለችው ።

እጅ በመንሳት አምንታውን ገለጸላት ። ሞላችለት ። ከዚያም ማንቆርቆሪያውንና ብርጭቆውን ውኃ ልክ ላይ አስቀምጣ ትእዛዙን በትጠባበቅ “ሌላ ሰው የለም?” የሚል ጥያቄ አንሙት ወረወረላት ።

“ለምን ?”

“የሚያግዘኝ ።”

“ለዚሁ ብዬ አይደል የመጣሁት ?”

“በግቢው ያላችሁት እርሳቸውና አንቺ ብቻ ናችሁ እንዴ ?”

“አይመለከትህም ። የመጣህበትን ጨርሰህ ውጣ”



አለችው በቁጣ ። አነጋገሯ እንደቁመናዋ ክርር ምጥን ያለ ኮስታራ ብጤ ናት ።

“ይብላኝለት አብሯት ውሎ ለሚያድር !” አለ አንሙት በሆዱ ።

በዝምታ ስራውን ጨርሶ አስረከባት ። በዝምታ ተለቃልቆ እጆቹን ሲያራግፍ “ጠላ ካስፈለገህ ፣ ያውልህ” አለች እንደተኮሳተረች ።

የዶሮ ዓይን የመሰለ ወፍራም ጠላ ስለነበር ሊግደረደር አልፈለገም ። አከታትሎ ሁለቱን ብርጭቆ በቁሙ እንደለጠጠ ክንፈ ብቅ አለለት ።

“ቆዳውን ውሰደው ። ለመንገድ ይኼ አይበቃህም” በማለት ዝርዝር ብሮች ሲሰጠው አንሙት በእጅ ነስቶ ተቀበለ ።

“አነሰህ ?”

“ኸረ ጌታዬ ! በቂዬ ነው ። እግዜር ይስጥልኝ ለአመት ሰው ይበልዎ!” የሚል ምርቃቱን አከሎለት ቆዳውን አነሳ —

“ስራ ፈላጊ ነኝ ብለሃል ።”

“አቤት ?” አለ አንሙት ። ጆሮውን አላመነም ።

ቋሚ ስራ ትፈልጋለህ ?”

“እንዴታ ጌታዬ !”

“ተያዥ አለህ ?”

“አለኝ ።”

“ነገ ጠዋት ብቅ በል ።”

“ተያዡን ይዤ ?”

“አዎ ።”

አንሙት እውነት አልመሰለውም ። እየፈነጠዘ ከክንፈ ግቢ ወጥቶ ወደ መርካቶ ገሠገሠ ። ቆዳውን በስድስት ብር ቸብችቦ ከቀን ገቢው ጋር አዳመረው ። የዚያን ዕለት ቀንቶታል ። ባገኘት አስራ ሶስት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም ምን እንደሚያደርግ እቅድ አወጣ ። በመጀመሪያ ድቅን ያለበት የአክፋይ ስጦታ ነው ። ከጉጃም ሲመጣ ላስጠጋው የሩቅ ዘመዱ አንድ ነገር ይዞ መሄድ እንደሚገባው ታየው ። በተያዥነትም ሊያቀርበው ያሰበው እርሱኑ ነው ። ዘመዱ ከእጅ ወዳፍ በሆነ ገቢ የሚተዳደር የፋብሪካ ሰራተኛ ቢሆንም ፣ የራሱን ጎጆ የቀለሰ ፣ ባለትዳርና የልጆች አባት እንደመሆኑ ለአንድ ጠርሙስ ካቲካላ መግዣ ሰባት ብር መደበለት ።

በርበሬ ተራ ፣ ከዋናው መንገድ ገባ ብላ ከምትገኘውና ከአምስት ደባሎቹ ጋር ከሚኖሩባት አንዲት ማድቤት ጐራ አለ ። በዚያን ዕለት ቀድሞ የገባው እርሱ ነበርና ሰሌኖቻቸው ተሐቅለው ከዋሉበት ጥግ አንድ በአንድ እያነሳ ካራገፈ በኋላ አቀጣቶሎ አነጠፋቸው ። የቀን ልብሶቹን በስርአት አጣጥፎ ትራስ አደረጋቸውና አሮጌ ብርድልብሱን ተከናንቦ ተጋደመ ።-ጓደኞቹ እየገቡ ቦታ ቦታቸውን ያዙ ። ሁሉም ሞቅ ብሎዋቸው ስለነበር ጐናቸው ገና መሬት ከመንካቱ እንቅልፍ ወሰዳቸው ። ሲገላበጥ ያደረው እርሱ ብቻ ነበር ።

ከሁሉም በፊት አንሙት ማልዶ ተነሳ ። ከመኖሪያቸው ፊት ለፊት ወደምትገኘው ሻይ ቤት ተሻግሮ ፊቱን በውኃ አበስ አደረገና ለቁርሱ ግንፍልፍል አዘዘ ። ተቆልሎ ቀረበለት ። ያን በሁለት ኩባያ ሻይ አወራርዶ እያገሳ ወጣ ።



ጠርሙስ ካቲካላውን ከየት እንደሚገዛ ወሰኗል ። በቀጥታ የሄደውም ወደ ወይዘሮ ሰውነቴ መሸታ ቤት ነው ። የአገሩ ሰው ናቸው ። አረቄያቸውንም የሚያስመጡት ከጐጃም እንደሆነ ይወራላቸዋል ። በዚህ ላይ ያያትን ሁሉ የምታማልል ምንታምር የምትባል ኮረዳ አሻሻጭ ስላለቻቸው ገበያቸው ምንጊዜም ሞቅ ያለ ነው ። አንሙት በየቀኑ ጐራ እያለ ፡ በተለይ ከምንታምር ጋር ፣ ዝምድናውን ካጠናከረ ቆይቷል ። ጠርሙስ ካቲካላውን ያለማስያዣ የለቀቀችለትም እርሷው ነበረች ።

ከዘመዱ ቤት የደረሰው የሩጫ ያህል በፈጠነ ርምጃ ነው ። እንደገባም ፡ ወጉ አይቀርምና ፡ ያልተነፋፈቁ ቢሆኑም ተሳሳሙ ። ዳቦና ጠላ ቀረበለት ። ዳቦውን ቀምሶ ጠላው እንዳይቀዳለት ተማፅኖና ወደ መጣበት ዋና ጉዳይ ገባ ። የትናንት ታሪኩን በዝርዝር ካወሳ በኋላ የአዎንታ ምላሽ በማግኘቱ በጣም ተደሰተ ።

በዚያኑ እለት ተያይዘው ወደ ክንፈ ቅጥረ ግቢ ሲዘልቁ ፡ ክንፈ በፒጃማው ላይ ጋቢ ደርቦ በረንዳው ላይ የጠዋት ፀሐይ ይሞቅ ነበር ። ያችኑ ገዴል ፊት ሠራተኛውን ጠርቶ ወንበር አቀረበችላቸው ። ዳቦና ጠላም መጣላቸው ። አንሙት ጠላውን የተጐነጨው ከብዙ መግደርደር በኋላ ነበር ። ለዚያውም ከአንዲት ብርጭቆ በላይ አልሄደም ።

ክንፈ የተያዡን መታወቂያ ወረቀት አይቶ ፡ አድራሻውን በማስታወሻ ላይ ከመዘገበ በኋላ ሦስቱም በፈረሙበት በአንዲት ብጣሽ ወረቀት የቅጥር ፎርማሊቲው ተከናወነ ። አንሙት ቀለቡንና መኖሪያውን ቀጣሪው ችሎለት ፣ ፀወር

ሃያ አምስት ብር ክፍያ ፣ ለአዲስ የህይወት ምዕራፍ በቃ ። የስራውን አይነት መዘርዘረ አላስፈለገም ። ዘበኛ ፣ አትክል ተኛ ፣ ተላላኪ ፣ … ሁሉንም መሆን እንደሚገባው ቀጣሪና ተቀጣሪ የተስማሙ ይመስላሉ ።

ክንፈ በሀይሉ ዋዛ ሰው አይደለም ። በእድሜው አርባዎቹን አመታት ለማገባደድ የተቃረበ ሲሆን ሃያ አም ስት አመታቱን በስራ አለም ያሳለፈ ነው ። ያልገባበት የመንግስት መስሪያ ቤት የለም ። የስራ ልምዱም የዚያኑ ያህል ሰፊ ነው ። ሲጀምር ተላላኪ ነበር ። የመዝገብ ቤት ፀሐፊም ሆኗል ። ከአንድ መስሪያ ቤት ወደ ሌላ የሚሸጋገረው በእድገት እየሆነ በአንድ ወቅት ረዳት ፐርሶኔልም እስከመ ባል ደርሶ ነበር ይባላል ። በመጨረሻም አሁን ባለበት ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ሽር ጉድ እያለ ነው ።

ክንፈ በምላሱ ጨፍ ይቆላል ። እንደ አብሮ አደጎቹ በቀለም ትምህርቱ እምብዛም አልገፋም ። ለአንቱታ ደረጃ የበቃው በጮሌነቱና በተግባቢነቱ ነው ። እርሱ 'ዲፕሎ ማሲ' ይለዋል ። የስራውንም ጠባይ በዚያ መስረርት አስቀምጦት ፡ ያጠመደ ሰው ከቢሮው አያገኘውም ። ሳምሶና ይት ሆርሳውን አንጠልጥሎ ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላው ሲሮጥ ፡ ከአንዱ ጋር ሻይ ፣ ከሌላው ጋር ቡና ሲል የጠዋቱን የስራ ሰአት አሳልፎ ከሆነ ከሰአት በኋላ እስካናካቴው ከዚያ ግቢ ደብዛው ይጠፋል ። ስራው ወደ ሌላ መስሪያ ቤት ወስዶታል ማለት ነው ።

የዘመን መለወጫና የገና በአላት በመጡ ቁጥር በርካታ



ካርዶችን አሳትሞም ይሁን አስገዝቶ ለአለቆቹና ወደፊት ሊተዋወቃቸው ላሰባቸው የሌሎች መስሪያ ቤቶች ባለ ሥልጣናት ይበትናል ። ለበአላቱ በሰላም በመድረሳቸው የተሰማውን ደስታ ከመግለጽ አልፎ ተርፎ በትጉህነታቸውና በሰራተኞቻቸው ዘንድ ባላቸው ተወዳጅነት ወደፊት ለታላቅ በታ የሚታጩ እውነተኛ የአገሪቱ ዜጎች እንደሚሆኑ ምኞቱ ንም በእርግጠኛነት ያሰፍርላቸዋል ። ሽንገላው የሚያስገኝለ ትም ጥቅም በዚያው መጠን ሰፊ ነው ።

ለማንም ሰው ሁል ጊዜ ሀሳቡ ሁሉ አይሳካለትምና ክንፈ አንድ ቋሚ ችግር አለበት ። ትዳር አልተዋጣለትም ። እንደ መስሪያ ቤቱ ፣ ሚስትም እድሜ ልኩን እንደቀያየረ ነው ። አንዷ ባማሟቀችው ቤቱ ሌላዋ ትገባበታለች ። እርሷም እግር በእግር በሌላዋ ትተካታለች ። ደግነቱ ከአንዳቸ ውም ልጅ አላፈራም እንጂ ቢያፈራ ኖሮ ቁጥራቸው በሽበቱ ልክ በሆነ ።

አንሙት ይህን የተረዳው ስራ በጀመረበት እለት ነው ። በፊትለፊት በር የተቀበላትን በኋላ በር መሸኘት የየእለት ተግባሩ ሆነ ። በዚህ ላይ ከሰራተኛይቱ ጋር ሊግባባ አልቻ ለም ። የቤቱ ፈላጭ ቆራጭ እርሷው ሆና ፣ ሲያሰኛት ኩርማን እንጀራ ትጥልለታለች ። ካላሰኛት ጠሙን አውላው ልታሳድ ረው ይዳዳታል ። አንዳንዴም ወደ ገበያም ሆነ ወፍጮ ቤት ስትሄድ እንደ ግል አሽከሯ የምታስከትለው ጊዜም ነበር ። እናም አንሙት የእንጀራ ገመዱን ላለማሳጠር ሲል ችሎ ማደሩን እንደሁነኛ አማራጭ ወስዶ ብዙ ታግሷል ። እንዲያ ማድረጉም ስለ ክንፈ ተጨማሪ ወሬ እንዲያገኝ ረድቶታል ።

"ለምን ትዳር አይዙም ?" አላት አንድ ቀን ፡ በመሀላ ቸው ሰላም ወርዶ በመጫዋወት ላይ ሳሉ ።

"ማግባት መፍታቱ ሰልችቷቸው ።"

"ታዲያ እንዲህ ሆነው እስከመቼ ሊዘልቁ ነው ?"

"እንጃ !"

"አንቺ እዚህ ቤት ስንት ጊዜ ሆነሽ ?"

"አመት ሊሞላኝ ነው ። ስገባም አንዲት ሴት ነበረች ፡ ሚስት ተብዬ ። የተለያዩት በቅርቡ ነው ።"

"ምን ይሆን የሚያጣላቸው ?"

"ሰውዬው ሁሌ ያመሻሉ ። ሲያሰኛቸውም በዚያው ያድራሉ ።"

"አሃ ! በሴቶቹ ጥፋት ያለም በይኛ !"

"እርሱን እርሳቸው ይወቁ ።"

"ለሰራተኞችስ እንዴት ናቸው ?"

ሳቅ አለችና "ደህና ናቸው" ብላው ተሽኮረመመች ። እንሙትም ነገሩ ገብቶት ፈገግ አለ ።

ይህን በተባባሉ ሰሞን አንድ ቀን ማለዳ ላይ እርሷም ንዚን ጠቅልላ ተሰናበተችው ። እንሙት ብቻውን ቀረ ። ቢሆንም ኑሮ አልከፋውም ። ቢችል ራሱ አብስሎ እንዲበላ ተፈቅዶለታል ። ከደሞዙ በተጨማሪ ከክንፈ እንግዶች የሚያገኘው የገንዘብ ጉርሻም የበሰለ ምግብ ፍለጋ ወጣ ማለት የሚያስችለው ነበር ።

ግቢውን በአትክልት ከማሳመሩም በላይ ልብስ አጥቦ የሚተኩስ ባለሞያ ነው ። የቤቱን ወለል በየቀኑ መስተዋት እስኪመስል ይወለውላል ። በንቁ ዘበኛነቱም የሚመሰገን



ሆነ ። በሽልማት መልክም በአንድ ዓመት ውስጥ አንድ አሮጌ ኮት ፡ ሁለት ሱሪዎችና ሦስት ሸሚዞች አገኘ ።

"እስቲ ሰራተኛ አፈላልግ" አለው ክንፈ አንድ ቀን ። "በደላላ የሚመጡት ጤና ቢሶች ሆኑ ።"

"እሺ ።"

"ተያዥ ያላት ፡ ቢያንስ በአበሻ ምግብ አሰራር ባለሞያ የሆነች ፡ ንፅህናዋን የምትጠብቅ" በማለት ሀሳቡን ሲሸርብ ቆይቶ "ፊቷ የፈካ" አለው ።

"ከፍትፍቱ ፊቱ ይባል የለ" አለ እንሙት ።

"አዎ ። የእጅ አመል ቢኖርባት ግድ የለኝም ። ልቆጣጠር ብልም አይሆንልኝማ ። እንደምታየው ቤቱ የእኩል ቤት ነውና ለዚያ የሚያደርሳት ጉትትም አይኖራትም ። ብቻ ነጭናጫና ነገር እንደ መስቲካ የምታላምጥ እንዳትሆንብኝ አደራ !"

"ግዴሎትም ! ሁነኛ ሰው እፈልግልዎታለሁ ።"

"አንተስ ፡ ቤቱ ተስማማህ አይደል ?"

"እግዜር እድሜዎን ያርዝምልኝ ። የጐደለብኝ ምንም ነገር የለም ።"

"በርታ ! በዚሁ ጠባይህ ከቀጠልክ ፡ ወደፊት ቋሚ የመንግሥት ስራ አፈላልግልሃለሁ !"

አንሙት ለጥ ብሎ እጅ ነሳ ። ቀኑ ቅዳሜ ነበር ፥ ከሰዓት በኋላ ።

"እና" አለ አንሙት "ከመቼ ጀምሬ ላፈላልግ ?"

"ዛሬውኑ መጀመር ትችላለህ" የሚል መልስ ስላገኘ ለመውጣት ወደ በሩ ሲንደረደር" "ቆይ ! እንዲት እንግዳ ስለምትመጣ ፥ እርሷን አስገብተህ ትሄዳለህ ።"

"እሺ ።"

የውጭው በር ስር በተለመደው ቦታው ተቀምጦ ሰራተኛ የት ብሎ እንደሚያፈላልግ ማውጣት ማውረድ ጀመረ ። የወይዘሮ ሰውነቴ አሻሻጭ ፥ ምንታምር ትዝ አለችው ። ምርጫውም በእርሷ አከተመ ።

ብትለብስና ብታጋጊጥ የሚያምርባት ፥ ትምቡኬ ገላ ናት ። ግምባሯና አገጭዋ ላይ ካሉት የመስቀል ንቅሳቶቿ በቀር ክንፌ ቤት ሲገቡና ሲወጡ ከሚከርሙት ኮረዶች የሚለያት ነገር የለም ። በዚህ ላይ ሳቋ ልብ ይሰርቃል ።

ይህን ሲያሰላስል ፥ በር አንኳክታ የገባችውን ወጣት የመዘናት በምንታምር ስእል ነበር ።

"ምንና ምን !" እያለ ተከተላት ። "ይህች ፀጉር ብቻ ናት ። በእርግጥ ዳሌዋ ከምንታምር ሰፋ ይላል ። ግን እግረ ሰላላ ፥ ቀትረ ቀላል ናት ።..."

በቀለም የተኾጎረጎረች አሻንጉሊት መሰለችው ። የቤቱን በር አንኳክቶ ለክንፌ ሲያስረክባት በሲጋራ የበለዙ ጥርሶቿን ብልጭ አድርጋለት "ቴንኪዩ !" አለችው በእንግሊዘኛ ።

"ከውካዋ !" ብሏት በሆዱ "መሄዴ ነው" አለው



ለክንፌ ።

"ሂድ ! ሂድ !" አለው ክንፌ ። ጊዜ ሊያጠፉ አልፈለገም ።

ከተሸለማቸው ሱሪዎችና ሸሚዞች ሻል ያሉትን አጥልቆ ኮቱን ደረበና ውልቅ አለ ። የበረረው በታክሲ ነበር። ከወይዘሮ ሰውነቴና ከምንታምር ጋር እንደ ስጋ ዘመድ ተቃቅፈው ተሳሳሙ ። ግብዣ አወረደላቸው ። እርሱ ግን አልቀመሰም ።

"ምነው ?" አሉት ወይዘሮ ሰውነቴ ።

"መድኃኒት ወስጄ ነው ።"

"ነገር አለሙን ረስተኸው እንደሁ ብዬ !"

"እዬ ! እንዴት ተብሎ ?"

"አምሮብሃል !"

"ይመስገነው !" አለ ወደ ጣራ አንጋጦ ። "ጥሩ ስራ አግኝቻለሁ ።"

"ጐሽ ! የት መስሪያ ቤት !"

"የሰው ቤት ነው ።"

"ምን ዐይነት ሥራ ? ዘበኝነት ?" አሉት ወይዘሮ ሰውነቴ

"አይ ! አትክልተኛ ነኝ ።"

"ደግ ! ደህና ይከፍልሃል ?"

"ቀለብና መኖሪያ ያስቡልኛል ። ደሞዙም አይከፋም ።"

"ታዲያ እንዲህ ጥፍት ይባላል ? ዘመድ አይጠየቅም ?" ምንታምር ነበረች እንዲያ ያለችው ፥ በናፈቀው ፈገግታዋ

እያማለለችው ።

"አልመች ብሎኝ" አላት ምራቁን እየዋጠ ።

አምና ለፋሲካ የወሰደውን የካቲካላ ጠርሙስ ሳይመልስ መቅረቱን ወይም ሂሳቡን አለመክፈሉን ሁለቱም ያስታውሳሉ ። ሆኖም ሰውነቱ ፊት ያን ማንሳት አልፈለጉም።

"ተጫወት" አለችው ምንታምር ።

"ምን ይዤ ?" አላት ። ለስላሳ መጠጥ ቤታቸው እንደማይገባ ያውቃል ።

"እርሷኑ !" አሉት ወይዘሮ ሰውነቱ ።

ምንታምር እንደማፈር ብላ "ቡና ላፍላልህ ? ወይስ ሻይ ?" ስትል ጠየቀችው ።

"ምንም አልሻ ፣ ካንቺ ወዲያ !" አለና አቀፋት ።

እየተሽኮረመመች ጐኑ ሻጥ አለች ። ወይዘሮ ሰውነቱም "መጣሁ" ብለው ከቤት ወጣ አሉ ። ሁለቱ ፍቀረኞች ብቻቸውን ቀሩ ።

"በሩን መለስ አርጊው ።"

"ሆሆ ! መሽተኛ ቢመጣስ ?"

"ከታዛ ይቆያ !" አላት እንደማይሆን እያወቀ ።

"አጣላኝ ከእቴቴ ጋር !" ስትል ተጐናደረችበት ።

"በይ ተይው ! ቀረብሽ !" ብሎ ጭንዋን ለመዘጋት ።

"በሽታ ይለምዝግህ !" በማለት ልትቧጭረው ጥፍሮቿን ስታሾልበት ሁለት እጆቿን ጥርቅም አድርጎ ሳማት ። ውኃ ሆና እንገቱ ስር ገባች ።



በሰመመን አለም ውስጥ እንዳሉ "ስራ ትፈልጊ ያለሽ ?" የሚል ጥያቄውን አቀረበላት ፣ በሹክሹክታ ።

"አግኝቼ!"

"ወይዘሮ ሰውነቱ ይለቁሻል ?"

"ይህን ካቲካላ እንደኑው ስትግፊ ከምታመሽ ፣ ምነው ቀንቶሽ በሄድሽልኝ ?ምትለኝ እርሷው ናት ። ጡት እናቴ ናት'ኮ !"

"ናቸው ? መች ይህን አውቄልሽ ! ተያዥም ይሆኑሻላ ?"

"እንኳን ለእኔ ለሌላም ትተርፋለች ።"

ስለ ክንፈ ቸርነት ፣ ስለቤቱ ሲሳይ ፣ ስለግቢው ማማር ሲዘረዝርላት ምንታምር አፏን ከፍታ ቀረች ። ግሳንግሷን አዝላ በዚያኑ እለት አብራው ብትሄድ በወደደች ።

እየተጐነታተሉ ስለራሳቸውም የወደፊት እድል አወሱ። በቅርቡም የመንግስት ስራ ይዞ ፣ ጐጆዋቸውን ቀልሰው ሰው ለመባል ሲበቁ ታይቷቸው በደስታ ተንሳፈፉ ።

በማግስቱ እንደሚወስዳት ወስነው ሲለያዩ ፣ ምንታምር መንገድ ድረስ ሸኘችው ። እንደአመጣጡ በታክሲ በሮ ክንፈ ግቢ ሲደርስ ጨለምለም ብሏል ። የውጭው በር ሲኮፈት የሰማው ክንፈ ሲንቆራጠጥ ቆይቶ ኖሮ ወደ በረንዳው ብቅ አለና "እህ ? የሄድክበት ቀናህ ?" በሚል ጥያቄ ተቀበለው ።

"አዎ ፣ ተያዥ ያላት ጥሩ ሠራተኛ አግኝቻለሁ ።"

"መልካም ፣ መች ታመጣታለህ ?"

"ከተመቸዎት ነገ ከሰዓት በኋላ ወይም ጠዋት ከረፋዱ

።”

“ጠዋት ይሻለኛል ። ከሰዓት በኋላ እንኳ ቀጠሮ ኝ ።”

“እሺ ፣ ማለዳ ሄጄ አመጣታለሁ ።”

ክንፈ ወደ ውጭ ለመውጣት የመኪናውን ሞተር ጓሙቅ ቆይቶ ወደ ቤት ሲመለስ አንሙትን ጠራውና ጣ ማለቴ ነው ። አመሽ ይሆናል” አለው ።

“እንግዳ ቢመጣስ ?”

“መጠበቅ ይችላል ።”

የክንፈ እንግዶች የታወቁ ናቸው ። አጠያየቁም ለይስ ላ ያህል እንጂ ምላሹም ያው የተለመደው እንደሚሆን ቃል ። ስራ በጀመረ ሰሞን ፣ እንደ ዛሬው ሳያረጋግጥ ፣ ት እንግዳ ተቀብሎ ሽርጉድ በማለት ላይ ሳለ ፣ ክንፈ እንግዳ ጭምር አለጊዜ በመምጣቱ በቤቱ ውስጥ ተፈጥሮ ረውን ፍጅት ሲያስታውስ ይዘገንነዋል ። ባስከተለው በዚያኑ ምሽት ከስራው የሚሰናበት ነበር የመሰለው ። ዴት እንደሆነ ባያውቅም ፣ አጅሬ ክንፈ በራሱ ሰላሙን ርዶ በማግስቱ ጠዋት ሁለቱን እንግዶች በአንድ ላይ ኛቸው በቅቷል ።

ክንፈ ከወዳጁ ጋር እንደወጣ ፣ አንሙት የግቢውን ራቶች አብርቶ ሲንቆራጠጥ አመሸ ። ጭልል ማለቱን ዶታልና አይጨንቀውም ። እያንጐራጐረ ግቢውን ር አድሮ ፣ እንቅልፍ የሚጥለው ንጋት ላይ ነው ።

ክንፈ እኩለ ሌሊት ገደማ ተመለሰለት ። እየሮጠ የመጣ ሉ ቁና ቁና እየተነፈሰ ከመኪናው ወረደ ። እንግዳ



አልነበረውም ።

“የመጣ ሰው አለ ?”

“የለም ።”

“ግልግል !” ብሎት ተለየው ።

“‘እንቺው ታመጪው ፣ እንቺው ታሮጪው’ አሉ ። እንዲህ ካስመረረው ለምን አይተወውም !” በሚል ትዝብት መግቢያው ድረስ በአይኑ ሸኘው ።

ጠዋት ክንፈ ቤቱን ሲከፍትለት ፣ አንሙት ሳሎኑንና መተላለፊያዎቹን ወልውሎ ካበቃ በኋላ ወደቀጠሮው ቦታ እንዲሄድ ፈቃድ ጠየቀ ። ለታክሲ አምስት ብር ተከፈለው ።

ወይዘሮ ሰውነቴና ምንታምር በጉዳዩ ተወያይተውበት ወስነው አድረዋል ። ቡና ተፈልቶለት ፣ ያን ፉት እያሉ ሲያወጉ ቆያይተው መጨረሻ ላይ ምንታምር ዞማ ፀጉሯን በኩኩስ ልጋና የክት ልብሷን አጥልቃ ተዘጋጀች ። የእንጨት ሳጥኗን አንሙት ተሸክሞላት ፣ ሦስቱም ተያይዘው ወጡ ።

የቅጥር ፎርማሊቲው ከአስር ደቂቃ በላይ አልወሰደባቸውም ። ቀለብ ከቤት ሆኖ በአርባ ብር ደሞዝ እንድትጀምር ተስማምተው ቤቱን አስረከቧት ክንፈ ወዲያው ውልቅ አለ ። ከዚህ ቀደም እንብዛም ባትጠቀምበትም ምንነቱን ታውቃለችና ምንታምር በመጀመሪያ መመገቢያ ክፍሉ ውስጥ ጥግ ላይ የተገተረውን ተለቅ ያለ ማቀዝቀዣ ከፍታ ተመለከተች ። የተከፋፈቱ የቆርቆሮ ምግቦች ፣ የተፈጨና የተቆራረጠ ስጋ ለየብቻ ፣ እንቁላሎች ፣ አትክልታክልት ፣ … ወዘተ. ታጭቀውበታል ። አብዛኛውን ስፍራ የያዘው ግን ቢራ ነው ።

ቀጥላም የጐበኘችው ማብሰያ ክፍሉን ሲሆን ፣ ይህም በብዙ መልኩ የተሟላ ነው ። አንዳንዱን እቃ ግን አጠቃቀሙን ቀርቶ አይታውም ስለማታውቅ ልትነካው አልፈለገችም ። ወደ ዋናው መኝታ ክፍል ገባች ። ከአልጋው ስፋት የአንሶላ ዎቹ ንጣት ፡ ከፍራሹ ትንቡኬነት የብርድልብሱና የአልጋ ልብሱ ልስላሴ ትንፋሿን ሰለበው ። በተመሳሳይ ውበት የደመቀ ሌላ አነስተኛ ክፍልም አጋጠማት ። የእንግዳ ክፍል መሆኑ ነው ። መፀዳጃ ቤቱን ፡ በስተጓሮ ዞራም የእርሷን መኝታ ክፍል ፡ የጢስ ቤትና የእቃ ማከማቻ ጓዳ ጐብኝታ ወደ እሉ፥ ተግባሯ እስክትመለስ አንሙት አልተለያትም ።

ከዚያም እየተረዳዱ የክንፈን መኝታ አንጥፈው እንዳ በቁ ምንታምር ምግብ ለማበሳሰል ወደ ማጀቷ ገባች ። አንሙትም መኪና ጋራዥ ውስጥ ወደተዘረጋው የእንጨት አልጋዉ ሄዶ ተጋደመ ። ጥሩ እንቅልፍ ወሰደው ።

ክንፈ ያለወትሮው ገና ለአይን ያዝ ሲያደርግ ቀሞሰበ ። ተከታዩ ቀን ሰኞ እንደመሆኑ እርሱም ጥሩ እንቅልፍ ሳይናፍቀው አልቀረም ። ምንታምር ከመኝታ ክፍሏ ስትሮጥ መጥታ እስከሚጠራት ድረስ ማብሰያው ክፍል ተቀመጠች ። ክንፈ በቀጥታ ወደመኝታ ክፍሉ ገብቶ ፒጃማውን ካጠለቀ በኋላ ቢራውን በብርጭቆ ሞልቶ ፉት እያለ ምንታምር ወዳለችበት ክፍል ዘው አለ ።

"ራት ላቅርብ ?" አለችው ከተቀመጠችበት ብድግ ብላ ።

"ምን አለሽ ?" ሲል ጠየቃት ።

"እንጀራ ስለሌለ ፡ የአትክልት ሾርባና ስጋ ጥብስ



አዘጋጅቼያለሁ ።"

"እ!" አለ ክንፈ በድንጋጤ ቅላፄ ። እንዲህ የሾረች አልመሰለውም ።

"ከዚህ በፊት ሰው ቤት ሰርተሻል ?"

"አዎ ፣ ባህርዳር ፈረንጆች ቤት ሰርቻለሁ ። ሰርተፊ ክም አለኝ ።"

"በወጥቤትነት ?"

"የተቀጠርኩት እንኳ በሞግዚትነት ነበር ። ሴትየዋ ምግብ አሰራር አስተማረችኝ ።"

"ለምን ወጣሽ ?"

"ፈረንጆቹ ወደ ሀገራቸው ሄዱ ።"

"ሌላ ቦታ ፣ አበሾች ቤትስ አልሰራሽም ?"

"እዚያም ሳለሁ ፣ አዲስ አበባም ከመጣሁ በኋላ ሞክሬ ነበር ። ..." ብላ ሀሳቧን አንጠልጥላ አስቀረችበት ።

"እናስ ?"

"የማይሆን ሆኖብኝ ተውኩት ።"

"እንዴት ?"

ምን እንደምትለው ግራ እንደተጋባች ሁሉ ፈገዛ ቀረች። ክንፈም መልሷን መስማት ስለፈለገ ጠረጴዛ ተደግፎ ቆመ ። አውጥታ አውርዳ "የሳው አመሉ ብዙ ነው ። አንዳንዱ ወጪውን ቆጥሮ ብዙ ነገር ያምረዋል ። አንዳንዱ ደግሞ በትንሽ በትልቁ ጭቅጭቅ ያበዛል ። አጠራቀሙልኝ ያልኳ ቸው ይመስል ደሞዜን በሰአቱ አልከፍል እያሉኝ ያስቸገሩ ኝም አሉ" በማለት ማብራሪያዋን ካቀረበችለት በኋላ ጣቶ ቿን እያፍተለተለች ወለሉ ላይ አይኖቿን ተክላ "እርግፍ

አድርጌ ቶቼው እቴቴ ዘንድ ተቀመጥሁ” ስትል ደመደመች።

“የጠዋቷ ሴትዮ ባለመጠጥ ቤቷ ?”

“አዎ ፣ የጡት እናቴ ናት ።”

“ደህና ፣ እኔ ቤት ያ ሁሉ ችግር የለም ። ለምሆኑ ራት በምንድን ነው ያበሰልሽው ?”

“በፈርኔሎ ።”

“በጋዝ ምድጃ አብስለሽ አታውቂም ?”

“እ ?” ድንግር ብሏት ። “በነጭ ጋዝ ነው የምትሉት?”

“ያ ሳይሆን በቡታ ጋዝ ።”

“በዚህ ?” አለችው አጠገቧ ወዳለው ምድጃ በጣቷ እየጠቆመችው ።

“አዎ ።”

“ፈረንጆቹ ቤት የዚህ አይነት ነገር አይቻለሁ ። ግን ሁሌም የምትለኩሰው ሴትዬዋ ነበረች ።”

“ጥሩ ፣ አጠቃቀሙን ነገ አሳይሻለሁ ።”

“እሺ” በማለት እጅ ነሳች ።

“ከእንጀራ ምጣድ በተጨማሪ ሌሎች በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እቃዎችም አሉ ። የእነዚያን ሁሉ አሰራር አሳይሻለሁ በቅርቡ ራስሽን ትችያለሽ ። ዋናው ነገር ቅንነት ነው ። ካወቅሽበት ቤቴ ቤትሽ ይሆናል ። አሁን ራት አቅርቢልኝ” ብሏት ወደሳሎን ተመለሰ ።

እንጀራ ከማስፋትና የዶሮ ብልት ከማውጣት በቀር ፣ ክንፈ በባልትና ከማንም ሴት አላንስም ባይ ነው ። ምንታምር ስልጡን ሆነችለት ። ሽርጧን ሽብ አድርጋ ሰሀኖቿን ፣ ሹካና ማንኪያዎቿን ፣ ከዚያም ሾርባውን በስሱ ከተቆራረጠ ዳቦ



ጋር ፣ አስከተላም ጥብሱን አቀረበችለት ። ክንፈ እያጣጣመ አስገባላት ።

“ሌላስ?” አላት ፣ በልቶ እንደጨረሰ እቃውን እንድታነሳሳ በጭብጨባ ጠርቷት ።

“ሌላስ የለም!” አለችው እንደማፈር ብሏት በአንድ እጇ አፏን ግጥም አድርጋ ይዛ ።

“ሞልቶ! አሁን አላስፈለገኝም እንጂ ፣ ሌላ ጊዜ ከፍራፍሬ ዐይነት ታስመርጭኛለሽ ። ሻይ ወይም ቡና ሊያስፈኝ ይችላል ።”

“እሺ” አለች አንገቷን እንደሰበረች ።

“ለአንሙት ራቱን ስጭው ። አንቺም በልተሽ በጊዜ ወደመኝታሽ!”

“እቃዬን አጣጥቤ ነው!” ስትል ቀልጠፍ ብላ መለሰችለት ፣ ሊታዘባት እንዳይሆን ሰግታ ።

“አሃ! ለካስ ያም አለ!”

ተከታዮቹ ጥቂት ወራት ለአንሙትና ለምንታምር የተድላና የፍስሀ ጊዜያት ነበሩ ። በአንድ ጣራ ስር አንድ አልጋ በመጋራት ባለትዳርነታቸውን ይፋ አያድርጉት እንጂ ተጋብተዋል ማለት ይቻላል ። የክንፈ መኝታ ክፍል የዘወትር መዝናኛቸው ነበር ። በእንግዳ መኝታውም ክፍል እንግዳ ሆነው ጋደም የሚሉበት ጊዜ አለ ። የእርሷም ሆነ የእርሱ መኝታ አይቆረቁራቸውም ።

እንሙትና ምንታምር በአፍላ ‘ትዳር’ እፍ ባሉ በአራተኛው ወር ፣ አንሙት በጊዜያዊ ሰራተኛነት ክንፈ መስሪያ ቤት አንገቱን አስገብቶ ሳያውቀው ቋሚ ሆነ ። ከክንፈ

ጥገኝነት ግን አልተላቀቀም ። ለመላቀቅም አልፈለገም ። ያለ
ደሞዝ የዘበኝነት ስራውን ቀጠለ ። ከመደበኛ ስራው መልስና
በእረፍት ቀናቱ የግቢውን አትክልት መንከባከቡን አላቋረ
ጠም ። ክንፈም ግልጋሎቱን ወዶለታል ።

ምንታምር አረገረገች ። ደምግባቷ ከእለት ወደ እለት
እየፈላቀ ሄዶ ሲያቅፍት የምትሟሟ ልዩ ፍጡር መሰለች ።
በአለባበሷና በፀጉር አሠራሯ ከከተሜዎቹ የማትተናነስ
ሆነች ። በስነምግባሯ ልዝብነት የተጠጓትን ሁሉ መግዛት
መቻሏ ሌላው መስህቧ ነው ። ክንፈን ከአንቱታ አላወረደች
ውም ። ለአንሙት ያላት ፍቅርም የሚቀዘቅዝ አልሆነም ።
ባጭሩ የምታሳሳ የቤቱ አዋይ ለመሆን በቃች ።

ታዲያ ጉዷን በጉያዋ ደብቃ እንጂ ልትፈታው ያልቻለ
ችው እንቆቅልሽም ሳይገጥማት አልቀረም ። ወገቧን ብትጠ
መጥምና የቀሚሶቿን ሽንሽን እየተረተረች ሆዷን ከተት
ለማድረግ ብትሞክርም እርግዝናዋ እያፈጠጠ መጣ ። ክን
ፈም አንሙትም ጠያቂዎቿ ነበሩ ። ከሁለቱም ጋር ስትንጐዳ
ጐድ እንደመቆየቷ ፣ ከማንኛቸው እንደፀነሰች አታውቅምና
ራሷው መስካሪም ዳኛም ሆና በረከቷን ለሁለቱም አደለቻ
ቸው ።

ክንፈ የአባትነቱን ምስራች በሰማ ሰሞን ሊያሰናብታት
አስቦ ነበር ። አይጣል እንዲሉ ፣ የምንታምር ፍቅር ፍርጃ
ሆነበት ። በዚያ ላይ ስሙን የሚያስጠራለት ፍሬ የማግኘቱን
እጣ ፣ በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ፣ እንደ ታላቅ ፀጋ
ቆጠረው። ስለዚህ በሚስትነት ባይፈልጋትም ፣ ማርያም
አለሁሽ ትበላትና ፣ ቀኗ ሲደርስ ወደ ጡት እናቷ ልኳት ከዚያ



እንድትገላገል ፤ ለማሳደጊያ በቂ ገንዘብ እንደሚደጉማትና
ሁለቱንም እንደሚንከባከባቸው ቃል ገብቶላታል ። እርሷም
ተስማምታለች ።

በአንድ ጐኑ ጉዳዩ በዚያ ያከተመ ቢመስልም ፣ በሌላ
ጐኑ ችግር አቈጥቁጧል ። ክንፈ ውሳኔውን የገለጸላት በጣም
ዘግይቶ ነበር ። እያመነታታ ልቧን ሲያዋልልባት በመክ
ረሙ፤ ምንታምር መጣያ እንዳታጣ በመስጋት ፍሬዋን ለአን
ሙትም አበርክታለች ። ‘የምስራች!’ ስትለው እርሱም
‘ምስር ብይ!’ ብሏት ያጠራቀማትን ጥሪቱን አሚጦ ልብስና
ጫማ ገዝቶላታል ። ዘዚህ ላይ ክንፈ ምንታምርን አለማባረሩ
እርግዝናዋ የማይመለከተው ቢሆን ነው ብሎ ገምቷል ።

እግዜር ሁን ያለው አይቀርምና አንድ ቀን ጉድ ፈላ ።
እለቱ እሁድ ነው ። ማለዳ ላይ አንሙት ክንፈ ዘንድ ቀርቦ
እየተቅለሰለሰ “የማማከርዎ ጉዳይ ነበረኝ” አለው ።

"ምንድን ነው?”

“ላደረጉልኝ ድጋፍ እግዜር አጠፌታውን ይክፈልዎ
እንጂ …መቼስ…እኔማ ምን ላደርግልዎ እችላለሁ?! እድሜ
ዎን ያርዝምልኝ! የልብዎን ይፈጽምልኝ!..” በማለት ምስጋ
ናውን ደርድሮ ለማለት የፈለገው አልወጣልህ ያለው ይመ
ስል በዝምታ ተቁለጨለጨ ።

“ምን እንዳደርግልህ ፈለግህ?”

“ጎዳ ብጤ ተከራይቼ ልወጣ አስቤያለሁ ።”

ክንፈ ደንገጥ አለ ። ያልጠበቀው ሀሳብ ስለነበር በቀላሉ
የሚዋጥለት አልሆነምና “ምነው? ምን ችግር ገጠመህ?”
አለው ።

"ኧረ ምንም ችግር አልገጠመኝም?"

"ታዲያስ?"

"እንዳው" አለ ሲፈራ ሲቸር፤ "ሰው ከማስቸገር ራሴን ልቻል ብዬ ነው ።"

"ቸገረኝ አልኩህ ?" አነጋገሩ የቁጣ ነበር ።

"አዬ ጌታዬ ! ጣጣው መች ከርሶ ሆነና!"

"ምን ታዲያ እዚያና እዚህ ትላለህ! መሄድ ከፈለግህ መንገዱ ያውልህ!" በማለት ወደ በሩ ጠቆመው ።

"ኧረ እንዲያም አይደል ።"

"እፉ! ውጣልኝ !" ሲል ክንፈ ጮኸበት ።

አንሙት ቆሌው ተገፍፎ ሹልክ ብሎ ወጣ ። ከክንፈ ጋር ሳይተያይ ውሎ አደረ ። ምንታምር በፈቃድ ወይዘሮ ሰውነቴ ዘንድ ውላ የተመለሰችው ማምሻ ላይ ነበር ። ከእርሷ ጋር እንደወትሮው ለመገናኘት አልቻለም ። ሀሳቡንም ቀደም ብሎ ፣ ካንዴም ሁለቴ ፣ አንስቶላት ስለነበር ባለመቃወሟ ተስማምታበታለች ብሎ አስቧል ።

ከክንፈ ጋር የተገናኙት ፣ በማግስቱ ሰኞ ክንፈ ቢሮ ውስጥ ነበር ።

"አቋምህን ባጭሩ ግልጽ አድርገህ ንገረኝ ። በትናንቱ ውሳኔህ እንደፀናህ ነህ?" አለው ክንፈ በቀጥታ ።

"አዎ ፤ አማራጭ የለኝም ።"

"ለመሆኑ ምን ችግር ገጠመኝ ልትል ነው?" በማለት ቱግ አለበት ። "እንደ ልብህ ትበላለህ ። የምትለብሰው አላጣህም ። ደሞዝህን እያጠራቀምህ ሰው ለመሆን ጥረት በማድረግ ፋንታ ቁልቁል ትመለሳለህ? አሁን በዚች ደሞዝህ ራስህን ትችላለህ?"



"ቆሎ ቆርጥሜም..." በማለት አንሙት የጀመረውን ሀሳብ ክንፈ አላስጨረሰውም ።

"ውጣ!"

"አያመናጭቁኝ እንጂ ጌታዬ ! ችግሬን አላወቁልኝ ምኮ!"

"ውጣልኝኮ ነው የምልህ! እንዲህ ያደረገህ ጥጋብ መሆኑን መች አጣሁትና!"

"አይደለም!"

"ታዲያስ? ምን ሊባል ነው?"

"ልጅቷ" አለ ራሱን እንደደፋ "መውለጃዋ ስለደረሰ ሸክም እንዳንሆንብዎ ብዬ ነው ።"

"የቷ?" ሲል ጠየቀው ። አዝማሚያው ሳይገባው አልቀረም ።

"ምንታምር ።"

"ምን!"

አንሙት መልስ አልነበረውም ። እንዳቀረቀረ በዝምታ ጠበቀው ። "ባለጌ! ልክስክስ!"

አንሙት ደሙ ፈላ ። ክንፈን ያስቆጣው ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም ።

"ውጣ!" ሲል አምባርቆበት "ምናምንቴ!" የሚል ስድብ ክንፈ አከለለት ።

"በህግ አምላክ !" አለው አንሙት ቀና ብሎ እያየው ።

"ግቢዬን ዛሬውኑ ለቀህ ውጣልኝ ። ከዚያም በኋላ እዚህ መስሪያ ቤት እንዳላይህ ። ማንነትህን የማታውቅ..."

"እንዴ!" አለ አንሙት በቁጣ ስሜት እየተንቀለቀለ ።

"እንዴት ማንነቴን አላውቀም ? ሰው ነኝ እኮ ፣ የሰው ልጅ!"

"ሂድ!" አለው ክንፈ በመጠየፍ ። "አንተም ከሰው ተቆጥረህ?! ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው? እስቲ ንገረኝ!"

አንሙት ንዴቱን መቆጣጠር አቃተው ። "አንተስ ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው?" በማለት በተራው ዘረጠጠው ።

የክንፈ ዓይኖች ተጉለጎሉ ። "ለስድብም ደረስክ?' ሲል ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳና እጆቹን ጨብጦ ወደ አንሙት ተንደረደረ ። አንሙትም ጡንቻውን አፈርጥሞ ቆየው ፤ ግብግብ ገጠሙ ፤ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት አንሙት ሀይሉን አሳየው ። ክንፈ ወደቀ ።

አንሙት ያለገላጋይ ቢሮውን ለቀለት "ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው ይበለኝ! እንደሰው ሰው ነኛ ! ሰው!" እያለ በደረጃው ቁልቁል ተንደረደረ ። ከቅጥር ግቢውም ወጥቶ ነጐደ ።

መንገዱን እንዴት እንዳገባደደው ሳይታወቀው ከክንፈ ቤት ደረሰ ።

ገና ከመግባቱ "ምንታምር!... ምንታምር!..." ሲል ተጣራ።

"ምነው ምን ሆነሃል?" እያለች ምንታምር ብቅ አለች ። አባረውት መደበቂያ የሚፈልግ ይመስል ሲርበደበድ አይታው ደነገጠች ።

"ይች ሴት አውል ሰደበኛ!" ብሏት ወደ ማደሪያው ሮጠ ። ምንታምር ተከተለችው ። "ማንነቱን የማያውቅ ፣



ምናምንቴ ይበለኝ?! እኔ አንሙት ቀን ጥሎኝ እንጂ..." እያለ ጨርቃጨርቁን በከረጢት ማመቅ ጀመረ ።

ጥሉ ከክንፈ ጋር እንደሆነ ምንታምር ገባት ። ግን የምትለው ጠፋት ። በድን ሆነች ። " 'ማነህ ቢሉህ ማነኝ ልትል ነው' አለኛ ! እኔም በአገሬ ሰው ነበርኩ" አለና የቀረቀበውን ትከሻው ላይ አድርጐ ተመለከታት ።

"ምን አጣላችሁ ?" ድንገት የመጣላት ጥያቄ ነበር ።

"ነፍሰጡር እንደሆንሽ ያውቃል ። ሸክም እንዳንሆን በት ቤትህን እንልቀቅልህ ማለት ይህን ያህል ያስደነፋል?" ሲላት ምንታምር ሰማይና ምድሩ ዞረባት ። ጉልበቷ ሲከዳት ታወቃት ። ተዝለፍልፋ መሬቱ ላይ ዘርፈጥ አለች ።

"እኔ በቃኝ ። ከመሰለሽ መሰንበት ትችያለሽ ። አሊያም ወይዘሮ ሰውነቴ ዘንድ ሂጂ ። የወደፊቱን እግዜር የውቅል ናል። ለፍሬ ብሎናልና ። እርሱው እንደሚያደርገን እንሆና ለን" ብሏት ውልቅ ሲል የጥላቸው መንስኤ እሷው እንደሆነች ምንታምር ተረዳች ።

ቃል ሳይወጣት በዝምታ ሸኘችው ። የህይወት ጉዳናዋ እየጨለመ ሲሄድ ታያት ። በሆዷ የያዘችው ፍጡር ውኃ ሆኖ ቢቀርላት ደስ ባላት ። የምታደርገው ጠፍቷት በጭንቀት ቁጭ ብድግ እያለች በሀሳብ ስትዋልል ክንፈ ከተፍ አለባት ።

የውጪውን በር ስትከፍትለት ፣ በመኪናው ሊገፈትራት ምንም ያህል አልቀረውም ። እንደወጣ በሩን ድርግሞ የተንደረደረው ወደ አንሙት መኝታ ቦታ ነበር ። እንደሄደ ተረዳ ።

"አንቺም ቅራቅርቦሽን አዝለሽ አሁኑኑ ውጪልኝ !

ምናምኒቱ ሁሉ!” ብሏት እየተጐናደረ ወደ ቤት ገባ ፡፡

ምንታምር እቃዋን ሸክፋ ግቢውን ለመልቀቅ እኩል ሰአተ አልፈጀባትም ፡፡ ሳትሰናበተው መሰስ ብላ ወጣች ፡፡

* * *

ይህ ሁናቴ በተፈጠረ በሦስተኛው ቀን ነበር አንሙት ወደ መሥሪያ ቤቱ ብቅ ያለው ፡፡ እንደማይሰነብትበት አውቋል ፡፡ በቀጥታ የሄደው ወደ ፐርሴኔሉ ቢሮ ነበር ፡፡ ከዚያም ወደ ክንፈ ክፍል ብቅ ብሏል ፡፡ በመጨረሻም መዝገብ ቤት ፡፡

‘ወፈፌው’ በለገሀር አካባቢ እየተዘዋወረ እስከዛሬ “ማነሀ ቢሉሀ ማነኝ ልትል ነው?” የሚል ፈሊጡን ያነበንባል ፡፡ ረሀብ በከረከረው ወገቡ ዙሪያ ትልታይ ጨርቆችን አጥብቆ ተብትቦ ሸቅብና ቁልቁል ሲጣደፍ ይውላል ፡፡ አንዳንዴም ይለምናል ፡፡ ግን ድርቅ አይልም ፡፡ ጠጋ ብሎ ሁለት እጆቹን አጋጥሞ ይዘረጋና አቀርቅሮ ምድር ያያል ፡፡ ከጣሉለት ጐንበስ ቀና እያለ ምስጋናውን ይገልጻል ፡፡ ካላገኘም እንዳቀረቀረ ወደ ሌላው ይሸጋገራል ፡፡ “እግዜር ይስጥህ!” የሚሉት ላይ ግን ያፈጥና አስደንጋጭ ሳቁን ለቅቆባቸው ‘ማነህ ቢሉህ’ ማነኝ ልትል ነው?” በማለት ያፋጥጣቸዋል ፡፡



# ጥብቅ መመሪያ

ረዥም ምንሽሩን በሆዱ አቅፎ ያደፈጠው ‘ጥበቃ—ጓድ’ ላቀው ከርቀት በሚያየው አጥር ላይ አይኖቹን ተክሏል ፡፡ በግራ እጁ ዳጎስ ያለ የካርኒ ጥራዝ ይዟል ፡፡ ከቀኝ ጆሮው መጋጠሚያ የገነፈለ ቢክ እስክሪፕቶ ብቅ ብሏል ፡፡

ግስላ ሲጋራውን እየሳበ ፤ ካቲካላ ያቦዛቸው አይኖቹን አጥሩ ላይ ሰክቷል ፡፡

ፀሃይ አዘቅዝቃለች ፡፡ ገበያተኛው ወደየቤቱ ይተማል ፡፡ አንዳንዱ ዕቃውን በኩሊ አሸክሞ ፤ የተረፈውን አንጠልጥሎ በድካም ተውጦ ያዘግማል ፡፡ ቅራቅንቦአቸውን አዝለው ፤ አሮጌ ጃንጥላቸውን ዘርግተው የሚያዘግሙ አሮጊቶችም ይታያሉ ፡፡ ...

ከንጋት ጀምሮ ምንም ያልቀናው ‘ጥበቃ—ጓድ’ በመሰላቸት እያፋሸገ አጥሩን አጥብቆ ይመለከታል ፡፡ የካቲካላ ሱስ እያቁነጠነጠው ‘ዲስኮ’ ሰዓቱን ተመለከተ ፤ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ትላለች ፡፡

‘ጥበቃ—ጓዱ’ ባተኮረበት አጥር ላይ ፤ ምንም እንኳ ቀለሙ ደብዝዞ ምን እንደሚል በውል ባይለይም ፤ ‘በዚህ አካባቢ መሽናት ክልክል ነው !’ የሚል ጽሁፍ እንደሰፈረበት ግምት የሚጭር አንድ የቆረፈደ ካርቶን ተንጠልጥሏል ፡፡ በዚያ አካባቢ ሲሸና የተገኘ እንዲቀጣ ለማድረግ የቀበሌው ጽህፈት ቤት አንድ ‘ጥበቃ—ጓድ’ መድቧል ፡፡ ይኸው የተመደበው ‘ጥበቃ—ጓድ’ ፤ ላቀው ፤ ደግሞ ስራውን

በጅመሪ ማግስት 'እዚህ መሽናት ከፈለጉ አምስት ብር መያዝዎን ያረጋግጡ !' የሚል ጽሁፍ ከደቃቅ ከሰል በተሰራ ቀለም ትንሽ ካርቶን ላይ አፅፎ ሰቅሏል ።

ላቀው አሁንም አጥሩ ላይ እንዳፈጠጠ ነው ። ተኩሶ የሚጥለው ጠላት ያጋጠመው ይመስል ከተቀመጠበት በድንገት እመር ብሎ አጠገቡ ከሚገኝ ምሽግ ውስጥ ገባ ።

ረሽም ምንሽሩን አነጣጥሮ "ቁም ! እንዳትንቃነቅ !" አለ ፣ የተጨፈነ አንድ አይኑን ወደ ማነጣጠሪያ አስጠግቶ ።

ከምሽጉ ወጥቶ እየሮጠ አጥሩ ላይ ሲሸና ወደነበረው ሰው ተጠጋ ።

"አምስት ብር ! … አምስት ብር !" እያለ ካርኒው ላይ ብዕሩን አሾለ ።

"የምን አምስት ብር ?" ሰውየው መሽናቱን አላቆመም።

"መሽናት ያስቀጣል ! ጥብቅ መመሪያ ነው !" አለው የካርኒውን ጥራዝ ገልብጦ በእስክሪፒቶው ፅጉሩን እያከከ ።

"ታዲያ እኛን ነው የምትቀጣው ?" አለና ሰውየው ሳቀበት ።

"ምን ትቀልዳለህ ? በህግ ! …"

"ንቃትህ ጥሩ ነው ። እኔ የዜሮ አንድ ሊቀመንበር የጓድ ሺመክት ዋሲሁን ታላቅ ወንድም ነኝ ። ዜሮ ሶስቶች በእርግጥ ጠንክራችኋል ማለት ነው ። የኛ ቀበሌ ጥበቃዎች እንኳ ፈዛዞች ናቸው ። ሃ … ሃ … ሃ … !" አለና ሰውየው እጁን ለሰላምታ ዘረጋለት ፣ ሸንቶ እንዳበቃ ።



"ምን እናድርግ ! አብዮቱ ጤናችሁን ጠብቁ ብሎ የለ ? ጤና መጠበቅ መመሪያ ነው" አለና ላቀው የተዘረጋለትን እጅ ጨበጠ ። …

ሰውየውን ለመቅጣት ባለመቻሉ እየተናደደ ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ አዘገመ ።

እለቱ ቅዳሜ ነበር ። ሁልጊዜ ቅዳሜ እንኳ ደህና ገቢ ነበረው ። በተለይም በአላማጣ ከተማ አካባቢ የሚገኙ ገበሬዎች ከገበያ መልስ ጠላ—ጠጅ ጠጥተው ወደየመንደራቸው ሲሄዱ አጥሩ ላይ የሚሸኑበት አጋጣሚ ብዙ ነው ። ሲሸኑ አድፍጦ የሚጠባበቀው ላቀው በዛቻና ግልምጫ አምስት … አምስት ብር ያስከፍላቸዋል ።

አብዛኞቹ ማስረጃ ወይም ደረሰኝ አይጠይቁም ፣ ለተቀጡበት ። የሚጠይቁ ካሉ ይሰጣቸዋል ። የካርኒውን ጥራዝ ፣ ይሰረቀው ወይ ወድቆ ያገኘው እንጃ ፣ ከአንድ እስክሪፒቶ ጋር ያስታቀፈው የዜሮ ሶስቱ ቀበሌ ሊቀመንበር 'ጓድ' ፀደቀ ነበር ። ካርኒው የታተመውም በ1952 ዓ.ም. ሲሆን በዚያን ወቅት ቤተክህነት ከምዕመናን መዋጮ የምትሰበስብበት ነበር ።

ላቀው ማይም ነው ። ስሙን እንኳ መፃፍ አይችልም ።

በዚህ ላይ መሠረተ ትምህርት በሚሰጥበት አካባቢ መድረስ አይወድም ። የሚያነሳበትም ጠላቱ ነው ። ያንገራገሩበት ወጣቶች ጥፌውንና እርግጫውን ፈርተው ትተውታል ። ስለዚህ ሊቀመንበሩ ራሱ በእያንዳንዱ ካርኒ አናት ላይ ታትሞ የነበረውን የቤተ ክህነት አርማ በጥንቃቄ ቆርጦ ጥሎ በምትኩ 'ጥብቅ መመሪያ' የሚል ፅሁፍ አስፍሮበ

ታል ። የከፋይ ስም በሚሞላበት ባዶ ስፍራ ላይ ደግሞ 'መሸናት ክልክል ነው ። የሸና ይቀጣል' ሲል ገጥግጦበ ታል ። የመቀጫው መጠንም በአህዝና በፊደል ተሞል ቷል ። ግን የቀበሌው ቁጥርም ሆነ ማህተም አይታይበትም ። እና የላቀው ስራ ለከፋይ ካርኒውን ከጥራዙ እየገነጠለ መስጠት ብቻ ሲሆን ብእሩን የሚያሾለው ለስሙ ነው ። ሁሉም በቅድሚያ ተዘጋጅቶ ቀርቦለታል ።

በቅጣት መልክ የሰበሰበውንም ገንዘብ ከአለቃው ጋር ይከፋፈላል ። ሁልጊዜ ቅዳሜ ቢያንስ ቢያንስ አስር … አስራ አምስት ብር አያጣም ነበር ። ዛሬን ግን አልቀናውም ።

እንደምንም ብሎ አምስት ብር እንኳ ማግኘት ነበረ በት ። የሰሞኑ የቤቱ ጭቅጭቅ ታየው ። …

"አሁን ትዳር ተብሎ ነው ?" ብላዋለች ሚስቱ ፣ ለተከታታይ ቀናት ፣ ሲገባና ሲወጣ ፣ ንትርክ አምሯት ምላሷን አሹላበታለች ።

"ምናለ ብትተይኝ ? እኔ ብር ልሁን ታዲያ ?"

"እኔስ ምን ልሁን ? አሁንማ ነብስ አባታችንም ተቆጡ ። በቀደም ቤተ ስኪያን ልሳለም ብሄድ ያሉኝን አልረሳውም ። እንዲህ እየተሳቀቅኩ ፣ የጉረቤት መሳቂያ ልሁን ? ወይእዳ ! … አየ እድል !" እየነፈረቀች ።

ነፍስ አባታቸው ቄስ መሀሪ አኩርፈዋቸዋል ። ባልና ሚስቱ ዝክር ብጤ የማያወጡ በመሆናቸውና ለአጥቢያቸው ታቦት ወርሃዊ—ክፍያ ባለማስገባታቸው በተደጋጋሚ ወቅሰ ዋታል ። ለነገ እሁድ አንድ ብር ከሃምሳ ይዞ እንድትመጣ ፣ ባታመጣ ግን ሌላ ነፍስ አባት እንዲፈልጉ አምረው ስለነገ



ሯት ተጨንቃለች ።

"ታዲያ ብር ከየት ይገኝ ? ዛሬ ማን ያበድራል ?"

"እንደምንም ብለሽ ፈልጊ ብለውኛል !"

"ድሆች መሆናችንን ዘንግተውት ነው ? ቀበሌውን እያገለገለ ነው አትያቸውም ? ካስፈለገ የትብብር ደብዳቤ ላጥፍ"

"የምን ትብብር ? ቤተስኪያን ውስጥ ቀበሌ ምን አገባው ? ደሞስ 'የነጣ ደብዳቤ ይዛ ሄደች !' ተብየ ጉረቤት ይሳቅብኝ !? 'ባለቤትሽ ቤተ ስኪያን አይሳለምም ። ሰንበቴ አይጠጣም …' እየተባልኩ መሳቂያ መሳለቂያ መሆኔ አንሶኝ ። …"

"ባንከፍል ምን ሊያደርጉን ነው ?" አላት ረዥም ምንሽሩን ቀባት በጠጣ ቁራጭ ጨርቅ እየወለዉለ ።

"ባንከፍልማ ስንሞት ማን ይፈታናል ? መቀበሪያ ቦታስ ማን ይሰጠናል ? እንደምንም ብለህ ብር ካምሳ ፈልግ ! አለዚያ ዋ !"

"እስቲ ደግሞ እሞክራለሁ ።"

"አስብበት ! ኋላ ይኸ ነገር እያዋጣንም !"

"ምን ዋጋ አለው ? መሰረተ ትምህርት የሚሉት [illegible] ከመጀመሩ በፊት ቅጣት ይገኝ ነበር ! ዛሬ ዛሬ ግን ሰው እያነበበ ነው መሰለኝ መሸናት አቁሟል ።"

"እኔ ነግሬያለሁ ! …"

"በቃ … ዝም በይኝ !"

ሚስቱ ከምትጠብቅበት ብር ከሃምሣ ሌላ ካቲካላ የሚቀምስበት ገንዘብ ያስፈልገዋል ። ሳይጠጣ ውሎ ግደር

አይችልም ። እናም አጥሩ ላይ ሸንቶ የሚቀጣ ሰው ለማግኘት ተስፋ አድርጎ ነበር ወደ ምሽጉ ያመራው ። እግረመንገዱንም ሁለት መለኪያ ካቲካላ የዱቤ ጠጥቷል ፣ በቁሙ ። ቢሆንለት በየቀኑ ካቴውን ፉት እያለና ባለ መረዋ ድምጿ አርሆ ድርብ ለገሰን እያደመጠ ፣ ከጓደኞቹ ጋር ሲያውካካ ቢውል— ቢያመሽ በወደደ ። አንዳንዴም ሞቀ ሲለው ግጥም እያቀበላት ፣ ጠጪዎችን እያስደሰተ ።

“አሥር ሣንቲም ያለው — አያዘረዝርም
ውጊያ የቀመሰ — ጡር አይናገርም ።
አይኑ መልከ መልካም — ጋሜነው ስሬቷ
የራያ መጋላ — መቃ ነው አንገቷ
በነላቀው ክልል — ዜሮ ሶስት ነው ቤቷ ... ” እያለ

አንድ ቀን ሲገጥምላት ፣ ጠጪው ጭብጨባውን አጋግሎለት በኩራት ተኮፍሶ ዙሪያውን መገላመጡ ፣ በሁለት ውጊያዎች ተካፍሎ ከሌሎቹ ‘ጥበቃ—ጓዶች’ ብልጫውን እንዳስመሰከረ መናገሩ ፣ ‘ትከሻየ ላይ ቆስያለሁ’ ብሎ በሞቅታ ግፊት ፣ አሮጌ ካኪ ሸሚዙን ገልብጦ የሆነ ጠባሳ ለጠጪዎቹ ማሳየቱ ከበሬታን አትርፎለት በተደጋገሚ ያንኑ ካቲካላ እንደተጋበዘ ሲያስታውስ የልቡ ትርታ ይጨምራል ። ...

በሀሳቡ ያን የደስታ እለት እያወጣ—እያወረደ በርቀት ያለውን አጥር ሲመለከት ብርድ ልብስ የተከናነበ ሰው አጥሩ ላይ ሲሸና አጋጠመው ።

ረኸም ምንሽሩን አቀባብሎ እያነጣጠረ “ቁም ! ... እንዳትነቃነቅ !” አለና በጉርናና ድምፁ አምባረቀ ።

አጥሩ ላይ ሲሸና የነበረው ሰው ወዲያውኑ አቋርጦ ፣



የቁምጣ ሱሪውን ቁልፎች ቆላልፎ መሬት የነካ ብርድልብሱን ሰብስቦ ወደ ተቀባበለው መሳሪያ ፊቱን መለሰ ።

“አትሽኑ ማለት ምን ማለት ነው ? አምስት ብር ተቀጥተሃል ! ብዙ የምታውቅ አይደለህም እንዴ ? በል ክፈል !” አለና ላቀው በገነፈለ እስክሪፒቶው ካርኒውን መወጋጋት ጀመረ ። ማማሰያ አንጂ ብእር የጨበጠ አይመስልም ።

“ምን አድርጌ ?” አለ ሰውየው ቆሌው ተገፎ ።

“የጤና ጠንቅ ሆነሃል ! እዚህ ለምን ሸናህ ? ጥሁፉን አንብብ ! ጥብቅ መመሪያ ነው” አለና አጥሩ ላይ ወደተንጠለጠለው የቆረፈደ ካርቶን አመለከተው ።

“እኔ ማንበብ የት እችልና ?”

“እሃ !” አለ ላቀው ዓይኖቹን በልጥጦ ፣ “ያም ተጨማሪ ቅጣት አለብሃ ! ለምን አትማርም ? ‘የማያነቡ ዓይኖች ቦታ የላቸውም ... አይኖሩም’ ሲባል አልሰማህም ? የአብዮቱ ሬዲዮ ነው እንዲህ ያለው ። ...ለዚህ ጥፋትህ ከሚደርስብህ ቅጣት እግዜር ያውጣህ ! አሁን ለሸናኸው ክፈል !” አለና ረኸም ምንሽሩን ከግራው ወደ ቀኝ እጁ አዞረ ። በተለያዩ ቁርጥራጭ ጨርቆች ከተጣጣፈው ፊልድ ጃኬቱ ኪስ ኮፊያውን አውጥቶ በራ ራሱ ላይ ደፋ ።

“ምህረት አድርግልኝ ! አይኔ በሽተኛ መሆኑን ታውቃለህ ። ... ” አለ ሰውየው በማስተዛዘን ።

“ስለ አይንህ የሚያገባኝ ነገር የለም ። በአይንህ አልሸናህ ! ባለመማርህ ከሚመጣብህ ጣጣ አግዜር ያውጣህ ብየሃለሁ ። አሁን ለሸናህበት ክፈል ! ጥብቅ መመሪያ ነው !

…" ካለው በኋላ ኮፊያውን አስተካክሎ ፡ ረዥም ምንሽሩን እንደገና ወደ ግራ እጁ አዞረ ፡ ዓይኖቹን እያጉረጠረጠበት ።

"ከየት ላምጣ ? የሚሸጥ የሚለወጥ የሌለኝ ድሃ ነኝ ። ተው አንተ ላቀው ! ወንድምህ ፡ ጐረቤትህ አይደለሁም ? በኔ ትጨክን !' አለና ሰውየው ተለማመጠው ። ተማፀነው ። ሚስጥር ኪሱ ውስጥ አጣጥፎ የሸጎጣትን አምስት ብር አውጥቶ ለችግር ከመዳረጉ በፊት ልመናውን ተያያዘው ። በዚች አምስት ብር ለአንዲት ልጁ ካኪ ጥብቆ ሊገዛ አቅዶ ነበር ።

"መመሪያ መመሪያ ነው ! በአብዮት ጊዜ ጐረቤት ፡ ጂኒ ቁልቋል የሚባል ነገር የለም ! አሁን አምስት ብር ትከፍላለህ ክፈል ! ካለዚያ ቀበሌ ትሄዳለህ ! ካድሬው ራሱ በአጠፌታ ያስከፍልሃል ፡ ያውም ከውርደት ጋር ! ካድሬ የሚላችሁን ተቀበሉ ብሏል አብዮቱ …ጥብቅ መመሪያ ነው" ብሎ ረዥም ምንሽሩን አንግቶ ፡ አምስት ጥይት ብቻ የያዘ አሮጌ ዝናሩን አስተካከለ ።

'ጥበቃ—ጓዱ' ላቀውና ሰውየው መኖሪያ ቤታቸው ቢራራቅ ጥቂት ነው ። ጥንት ጀምሮ ይተዋወቃሉ። ሰላምታም ነበራቸው ። ላቀው 'ጥበቃ ጓድ' ከሆነ ወዲህ ግን ባህሪይው በመለወጡ ብዙ ሰው ሸሽቶታል ። የታጠቀው መሳሪያ ምላሱን ያረዘመለት ይመስል ማንገት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ ነገር ነገር ይለዋል ። መኮሳተር አብዝቷል ። በተለይ ኮፊያውን ደፍቶ በሚንቀሳቀስበት ወቅት በእለት ጠብ የተፋጠጡ ሰዎች ሲያጋጥሙት እንኳ ለመገላገል መሃላቸው ዘሎ የሚገባው 'ጥብቅ መመሪያ ነው !' በሚል ማስጠንቀቂያ



ሆኗል ።

"ትከፍላለህ አትከፍልም?" ላቀው አምባረቀበት ።

"መረኝ ነው ያልኩህ ላቀው!" አለና ሰውየው ጉል ቱን ሊስም ጉንበስ ሲል ላቀው ወደኋላ አፈግፍጎ "ጤ አለህ?" አለና አፈጠጠበት ።

"ድሃ ነኝ! የዛሬን እለፈኝ!"

"የምንድሃ? ለአብዮቱ የማይገዛ ድሃ ድሃ አይደለም! 'ድሃ ሁለት አይነት ነው' ብሏል ጓድ ጠደቀ ። 'አንዱ ጭቁን ድሃ ፡… ሌላው ደግሞ ዝም ብሎ ድሃ ።' ክፈል ። ጥብቅ መመሪያ ነው…!"

"ዋስ ልጥራልህ ሰርቸ ልክፈልህ?"

"የአብዮቱን ህግ የጣሰ ዋስ አይጠራም!"

"እረ ተለመነኝ ! ወደ ስራየ ልሂድ!" ሰውየው አይ ኖች እንባ ማቅረር ጀምረዋል ።

"የምን ስራ? ከሁሉም በላይ ለአብዮቱ! ብሏል ወጣት አዛውንቱ ።"

ሰውየው ጭንቅ አለው ። የሚያደርገው ጠፋው ። ምን ቢለው ምህረት ሊያገኝ እንደሚችል ማሰብ ተሳነው ። አምስት ብርን ያክል ነገር ጨክኖ ሊሰጠው አልደፈረም ። የማይለቀው መሆኑንም ተገንዝቧል ። ላቀው ከበየነበት አምስት ብር ቀንሶ ሊከፍለው ወሰነ ።

"ሁለት ብር አለኝ ላቀው!…አንተም ወደህ አይደለም ፤ ታዘህ ነው" አለ በሚያግባባ አነጋገር ።

"የምን ሁለት ብር? ትቀልዳለህ? ጥብቅ መመሪያ ነው! በዚህ ቀልድ የለም! 'ቀልድ የለም በአብዮቱ' ያለው ጓድ

ጠደቀ ነው ። ጓድ ጠደቀን አታውቀውም? መመሪያ አትቀበልም ? የቀበሌያችን ሊቀመንበር ጓድ ጠደቀ ዋዛ ሰው አይምሰልህ ! ቀለም ግልብጥ አድርጎ የጠጣ ምሁር ነው! ይሻልሃል ! ዋ! … ጥብቅ መመሪያ በሚጥስ ሰው ላይ እርምጃ እንድንወስድበት አስጠንቅቆናል!”

“እሺ ሶስት ብር ይሁን!” አለ ሰወየው ደንግጦ ። ‘እርምጃ’ የሚባል ቃል ሲሰማ ከመቅጽበት ተሸበረ ።

‘ጥበቃ ጓዱ’ ላቀው ከካርኒው ጥራዝ አንድ ቅጠል ካርኒ ገንጥሎ ወረወረለትና ያነገተውን ረዥም ምንሽር ከትከሻው አውርዶ ላይ ታች ተመለከተው ።

“ኧረ ስለእግዜር ብለህ…” በፍርሃት የተሸበረው ሰውየ የመጨረሻ እድሉን ሞከረ ።

“ይችን ይወዳል ላቀው !” አለ ላቀው በረዥም ምንሽሩ ሰደፍ ከመሬት ሊደባልቀው እየቃጣው ።

ሰውየው ምንም ማድረግ አልቻለም ። ማንባት በጀመሩ አይኖቹ እየተመለከተው ከሚስጥር ኪሱ ድፍን አምስት ብሯን አወጣና ሰጠው ።

“ካርኒህን ያዝ!” ብሎ የቀደደውን ካርኒ አስጨበጠው። ቀጠለና “ካርኒ ማስረጃ ስለሆነ መጥፋት የለበትም ። ጥብቅ መመሪያ ነው ። መታወቂያ ወረቀትህን ከኪስህ አትለይ! ቀበሌያችን በዚህ በዚህ እንዲበለጥ አንፈልግም ።… ለዞር አንዶች ምሳሌ መሆን አለብን!” ሲል ቀባጥሮ ኮፊያውን ወደ ቅንድቦቹ ዝቅ አደረገና ቁል ቁል ወረደ ።…

ሰውየው አመልካች ጣቱን ሽቅብ ቀስሮና በጉም ወደተሸፈነው ሰማይ አንጋጦ “ኤህ!…” አለ በምሬት ።



“ሃምሣ ሳንቲም መልሺልኝ! ” አለ ላቀው አጉንብ
የጠላ ጋን ለምታለቀልቀው ሚስቱ ሁለት ብር አውጥ
እየሰጣት ። “ ቶሎ በይ አትቀላምጂ!” ግስላ ሲጋራው
ልምጥጥ አድርጎ እየሳበና እየተኮሳተረባት ።

መሸታ ቤቱ በጠጪ ግጥም ብሏል ። አርሆዋ ድርብ
ለገሰ ታቅራራለች ፣ በማሲንቆ እየታጀበች ።

ላቀው እንደገባ ጥግ ያዘና የተቀዳለትን ሁለት መለኪያ
ካቲካላ በሁለት ትንፋሽ አጋብቶ አጨበጨበ ። ሌላ ግስላ
ሲጋራ ለኩሶ ዙሪያ ገባውን ከቃኘ በኋላ “በዕብዮት ጊዜ
የለም ትካዜ ! ተቀበይ!” አላት በቁሟ እየተወዛወዘች
የምታቀነቅነዋን አርሆ ። ፊቷን ወደሱ መልሳ ፈገግ እያለች
ስትጠቅሰው ላቀው በኩራት ኮስተር አለና

“አሥር ሣንቲም ያለው — አያዘረዝርም
ውሂያ የቀመሰ — ጡር አይናገርም

እንደሰት እንጂ — እድሜ ለጠደቀ
ዜሮ ሶስት መብለጡ — በአገር ከታወቀ ።

እህል ውሃ ሞልቶ — ከተረፈ ወጡ
ከዜሮ አንድ ልጆች — ዜሮ ሶስት በለጡ!”

ጠጪው ጭብጨባውን አቀለጠው ። በውስጡ እግሩ
ወለሉን ተመተመው ። ላቀው በኩራት ተሞልቶ የካቲካላ
መለኪያውን ሲያነሳና ሲያስቀምጥ አመሸ ።…

የሌሊቱ ሮንድ ተረኛ ስለነበር የራሱንና ለአርሆዋ
የጋበዛትን የሁለት መለኪያ ካቲካላ ሂሳብ ከፍሎ አፋ

እየጠራረገ ወጣ ፣ ከሌሊቱ አምስት ሰዓት ላይ ።

አካባቢው በጣም ከብዷል ። በዚያ ድቅድቅ ጨለማ የሚንቀሳቀሱ ቢኖሩ የሌሊቱ ሮንደኞች ብቻ ናቸው ። ሰአት እላፊው ሶስት ሰአት ነው ።

ረዥም ምንሽሩን አቀባበለና አመልካች ጣቱን ቃታው ላይ አሳርፎ ሽቅብ ቁልቁል ማለት ጀመረ ። ከሌሊቱ ተረኛ ጓደኞቹ ጋር መደባለቅ አልፈለገም ። ከሰዓት እላፊ በኋላ ሲዘዋወር ከሚገኝ ሰው ብዙ ነገር ይገኛል ። ስለዚህም 'ጥበቃ ጓዶቹ' በየግል መሰማራትን ይመርጣሉ ፣ ጥቅም ላለመካፈል።

ላቀው ሮንድ በሚወጣበት ግዜ ሌላም አመል አለው ። ሴተኛ አዳሪ ቤት ያድራል ። ዞርዞር ሲል ይቆያይና ከአይኑ የገባችለትንና ቀን ያሰባትን ሴተኛ አዳሪ ቤት ይቆረቁራል ። ሴተኛ አዳሪዋ ወንድ የያዘች ቢሆንም ደንታው አይደለም ። ሰውየውን 'ትፈለጋለህ!' በማለት በፈጠራ ወንጀል አስደግድጎ ያባርረውና ሴትዮዋን አቅፎ ያድራል ።

ለዛንለቱ ያሰባት ደግሞ ባለጠጅ ቤቷ አማረችን ነበር ። ባለንቅሳታሟና ዘርቦጥቦጥ ያለችው አማረች ልቡን ሰርቃዋለች ። እስከ ሌሊቱ ሰባት ሰአት ድረስ ከተዘዋወረ በኋላ ሳርቀበሌ አካባቢ ትልቁ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳ አጠገብ ከሚገኘው ጠጅ ቤቷ ሄደ ።

በሯን አንኳኳ ። በቤቷ ውስጥ ጭል ጭል ስትል የነበረችው የፋኖስ መብራት እስከናካቴው እልም አለች ። በሯን ደግሞ እንኳኳ ።

ሳል የሚያስረቀርቀው የወንድ ድምፅ ከወደ ውስጥ



ሲሰማ ላቀው ደረቱን ነፋ ።

"ክፈቱ! አማረች…ሮንድ ነን!" አለና ደጋግሞ አንኳኳ።

"ምንድነው? ማነህ?" በበሩ ስንጥቅ አፎሙልቃ ተመለከተችው ፡ አማረች ።

"ላቀው ነኝ!… ጓድ ላቀው! ክፈቺ!"

"ለምን?"

"ክፈቺ ማለት ምንድነው?" የተቆጣ መሰለ ። ድምጿን አጠፋች ።

"ትከፍቺያለሽ ክፈቺ! የሚፈለግ ሰው ቤትሽ ውስጥ አለ ።" በረዥም ምንሽሩ አፈ ሙዝ በሩን ደበደበው ።

"እንዴ? በህግ!… እሪ እላለሁ!"

"ክፈቺ ፤ ሰውየው ይፈለጋል!"

"ማንም ሰው የለም!"

"እየደበቅሽው ነው? ጥሩ ! ፀረ አብዮተኛ ነው ብያለሁ… እሱ አያዋጣሽም!… ጥብቅ መመሪያ ነው!" ብሎ ሲዝት በሩ ብርግድ ብሎ ተከፈተ ።

"እኔ ነኝ ተፈላጊው? ማነው ፀረ አብዮተኛ ?…" እያለ የሚደነፋ አንድ ሰው ሽጉጡን ደግኖ አፈጠጠበት ። የቀበሌው ሊቀመንበር 'ጓድ' ፀደቀ ነበር ። ላቀው ኩምሽሽ አለ ።

"ኧረ በስተት ነው…ጥቆማ ደርሶን ነበር! ለዚያ ነው የመጣሁ ። ይቅርታ! " አለ ላቀው እንደተሽማቀቀ ።

ፀደቀ የላቀውን ረዥም ምንሽር መንጭቆ ነጠቀውና ከጀርባው ሽጉጡን ደግኖበት ፊትና ኋላ ሆነው ጥቂት እንደሄዱ "ኧረ ማረኝ … ጓድ ጠደቀ! ሂሴን ውጫለሁ…"

አለ ላቀው በመርበቅበቅ ።

"ቀጥል!" በሽጉጥ አፈሙዝ ጭንቅላቱን አለው ። ፊቱ በደም የተሸፈነው 'ጥበቃ ጓድ' ላቀው መቀጠል አልቻለም ። ተንገዳገደና ኸዋ ብሎ መሬቱ ላይ ተዘረረ ።

"ትነሳለህ አትነሳም?"

መልስ የለም ።

"ተነስ! ሌላ አላማ አለህ ማለት ነው!?" ላቀው አልተንቀሳቀሰም ።...

በአጠገባቸው ማንም አልነበረም ። ፀደቀ ከበላዮቹ ሊመጣበት ከሚችል ጣጣ ለመዳን እየተጣደፈ ሲሮጥ ከሌላ ባለ ዲሞትፎር ' ጥበቃ ጓድ' ጋር ተገናኘ ።

"ምንድነው ጓድ ጠደቀ?" አለው ባለ ዴሞትፈሩ በተጠንቀቅ ቆሞ ።

"ላቀው ተመትቶ ወድቋል ። ማን እንደመታው እንጃ ። ይቺ ነገር ዋ!" አለና እያለከለከ "እኔ ሪፖርት ላደርግ መሄዴ ነው ። አንተ ደጋግፈህ ከቤቱ አድርሰው! ጥብቅ መመሪያ ነው!" ብሎት ፀደቀ ግራ ቀኝ እየተገላመጠ ዋናውን ጐዳና ይዞ ሽቅብ ወጣ ።

ባለ ዲሞትፈሩም 'ጥብቅ መመሪያ' የምትለዋን ሀረግ እያነበነበ በተጠቆመው አቅጣጫ ላቀውን ፍለጋ ሄደ ።...

የ 'ጥብቅ መመሪያ' ው መዘዝ እንደሚጠመጠምበት አልጠረጠረም ።

* ሚያዝያ, 1983
መቀሌ



# ስጋ ብፃት

ዶፍ እየወረደ ፣ ነጐድጓድም አካባቢውን እያናወጠ ባደረበት የነሐሴ ወር መባቻ ላይ በሀይቅ ግንባር በኩል ቅልጥ ያለ ውጊያ ይካሄዳል ። የቢኤም አስፈሪና አስደንጋጭ ግምግምታ ፣ የታንክና የመድፍ ድምድምታ ፣ የመትረየስ እሩምታና የክላሽን ካካታ ፣ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ምድር ቀውጢ ሆናለች ።

ከሀይቅ ከተማ ወደ ውጫሌ በሚወስደው መንገድ ላይ አምስት ኪሎ ሜትር ያክል ርቃ በምትገኘው ትንሽ ጅረት አጠገብ ተኩስ ቀልጧል ። ፍልሚያው ተፋፍሟል ። ውጪ ነፍስ ፣ ግቢ ነፍስ ሆኗል ። ህይወት ያልፋል ። ጣእር ሰፍኗል ።

አፈሙዝ በተኩስ ግሎ ፣ ሳንጃ በደም ተጨማልቆ ፣ ደም እንደጅረት እየተንኳለለ እንደ እርጎ ሲረጋ ፤ በሚንዥርቀቀው ዶፍ የረጋው ደም እየቀጠነ ብርዝ መስሎ ሲወርድ ፣ ጀግና ወድቆ 'ውሃ ውሃ' ሲል ፤ ጠብታ ውሃ አፉ ላይ የሚያደርግለት አጥቶ እያቃሰተ የህይወት ክሩ እስክትበጠስ በሲቃ ሲጠባበቅ ፤... የሚታየው የሞት ዋዜማ አስፈሪ ድባብ ሰው ሆኖ መፈጠርን ያስጠላል ።

ከትንሿ ጅረት አጠገብ ባለው ሰፊ ረግረጋማ ቦታ ላይ ያለችው አንዲት ጐፈሬ ወጣት ሌሊቱን በሚወርደው ዶፍ ክፉኛ በስብሳለች ። ክላሽን ብረቷን በደረቷ አቅፋለች ። ሚዛን የሚደፋው የጥይት ትጥቋ በሽንጧ እንደዞረ ነው ። ከሷ አነስ የሚል ወጣት ተሸክማ ረግረጋማውን ቦታ ለማቋረጥ ትዳክራለች ።

በዚያ ድቅድቅ ጨለማ የሚታያት አንድም ነገር የለም። የሚታያት ነገር ቢኖር የከባድና የቀላል መሳሪያ ጥይቶች ለአካባቢው የሚፈጥሩት ውጋገን ብቻ ነው ። ያም ብዙ አይቆይም ። ከገባችበት ረግረግ ተራምዳ እንድትወጣ አልረዳትም ።

ሰውነቷ ዝሏል ። ብርክ ይሰማታል ። የምትቀናንሰው ሸክም ስላልነበራት በዛለ አቅሟ ረግረግ ውስጥ ትንከላወሳለች ። እስከ ጉልበቷ ድረስ በጭቃ ተውጣለች ። ፕላስቲክ ጫማዎቿን ውጦ ስላስቀረባት የምታዘግመው በባዶ እግሯ ነው ።

የተሸከመችው ወጣት ደግሞ "ው … ሃ !" እያለ ያቃስታል ። ቁስለኛ ነበር ።

የቆሰለው ትከሻው ላይ ነው ። ብዙ ደም ፈሶታል ። በከባድ ድካም ከመዝለፍለፉም በላይ ቁስሉ እየጠዘጠዘው መሆኛውን አሳጥቶታል ። በምን ሁኔታ ላይ እንዳለም የሚያውቅ አይመስልም ። ጉሮሮው ደርቋል ። እና በተደጋጋሚ የተሸከመችውን ወጣት 'ውሃ ! … ውሃ !' እያለ ያስቸግራታል ።

እግሮቿን አላራምድ ያለው ረግረግ አሸንፎ ሊጥላት ደረሰ ። ጉልበቶቿ ተብረከረኩ ። ብርዱ ፣ ነፋሱ ፣ ዝናቡ ፣ ረሃቡ ፣ ጥማቱ ፣ ድካሙ ተዳምረው ፍፃሜዋን አቀረቡት ።

ተስፋ ግን አልቆረጠችም ። ጥርሷን ነክሳ ግብ ግብ ገጥማለች ። "ውሃ … ው … ሃ !" ድክም ባለድምፅ ነበር የተናገረው ፣ ቁስለኛው ።

"እ … ሽ!"



ከረግረጋማው ቦታ ወጥታ ቀና መንገድ ለመግባት አቅጣጫዋን ለወጠችና በሰያፍ አዘገመች ። የአሁኑ ይሻላል ። ረግረጉ ቀንሷል ። ጥልቀት የለውም ። ጭቃው እንዳያዳልጣት ብቻ በጥንቃቄ እየረገጠች ጥቂት እንደገፋች አንድ እሾሃማ አጥር ውስጥ ተመስገች ። ቁስለኛው ስቃዩ በዛበት ። አቃሰተ ። ወደኋላ ስታፈገፍግ ሁሉም ነገር ከአቅሟ በላይ ሆነባት ። ሸክሟን የመቀነስ ግዴታ መጣባት ። ቁስለኛውን ወጣት ቀስ አድርጋ አውርዳ ምድር ላይ አሳረፈችው ። በደረቷ አቅፋው የነበረውን ክላሽን አውርዳ አስቀመጠችው።

ቁስለኛውን ከወገቡ ቀና አድርጋ ጭንቅላቱን ግራ ጭኗ ላይ አሳረፈችለት ። አቡጀዲ ተልትላ ያሰረችለት ትከሻውን ዳበሰችው ። እስሩ ላላ ብሎ ነበር ። አጠበቀችለት ። ወዲያው ድካም ደፋ ቀና ያደርጋት ጀመር ። ከቁጥጥሯ ውጪ በሆነ ኃይል አሸለበች ። …

ተኩሱ እንደተጋጋለ ነው ። የሟች ቁጥር በሁለቱም ወገን ተበራክቷል ። ከተኩሱ የባሰው ነጐድጓዱ ነበር ። ምድርን ለሁለት የገመሳት የሚመስለው አሸባሪ ድምፁን በተደጋጋሚ ይለቀዋል ።

"ኧረ ውሃ ! … ውሃ!" ቁስለኛው ደመ ነፍሱን ተናገረ ። በሸለብታ ላይ ያለችው ወጣት ግን አላደመጠችውም ። ብታደምጠው እንኳ በዚያ ቅልጥ ባለው የሞትና የሽረት ፍልሚያ ምላሽ የምታገኝለት አልነበረችም ። ዋናው ተግባሯ ቁስለኛውን ህክምና እንዲያገኝ ባለ በሌለ ሃይሏ ተሸክማው ውጫሌ ማድረስ ነው ፣ ተስፋዋ ይኸው ነው ።

አቅሙ እንደማይኖራት ብታውቅም ፣ እስከተቻላት ገፍታ በት የሚያግዟት ሀይሎች እንደማታጣ ተማምናለች ።

የወገኖቿ እቅድ አጥቅቶ የመመለስ በመሆኑ ንጋት አካባቢ በሚሰጠው ልዩ የተኩስ ምልክት ከውጊያው ጐራ በሀይወት ማምለጥ የቻሉት ወደ ውጫሌ ይመለሳሉ ። …

ቁስለኛው የጣር ድምፅ አሰምቶ ሲንፈራገጥ ባነነች ። ጆሮዋን ልቡ ላይ ለጥፋ አዳመጠች ። ልቡ እየዘገየች ድው … ድው … ትላለች ። በሕይወትና በሞት መካከል እንደሚገኝ ተገነዘበችና ምን ማድረግ እንዳለባት ማሰብ ጀመረች ።

ስንት ሰአት ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ሞከረች ። እንቅስቃሴ የተጀመረው ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ላይ ነው ። ሰባት ተኩል ላይ ውጊያው ተጀምሯል ። ውጊያው ለሁለት ሰአታት ያክል የተካሄደ ሲሆን አሁን ዘጠኝ ተኩል ከሌሊቱ ሆኗል ማለት ነው ። ለአስር ሰአት ሩብ ጉዳይ ደግሞ መልስ ይሆናል ።

ከላሸኑን እንስታ ደረቷ ላይ አጋደመችው ። ቁስለኛ ውን ልታነሳው ስትሞክር ፣

"ተይኝ ! አንድ ግዜ ብቻ … ትንሽ !" አለ ።

"ተው እስቲ አንተ ጓድ ! ቀና በል ባክህ ! … አግዘኝ እንጂ !" አለችና ተሸክማው ማዘገሟን ቀጠለች ።

ተኩሱ ተጧጡፎ ፣ ከወዲያኛው ወገን የተተኮሰ ቤን ጋል ላይት በፈጠረው ብርሃን አካባቢዋን ቃኘች ። አቅጣጫ ዋን ስታለች ። ከፍተኛ ድንጋጤ ቢሰማትም ያላትን ሃይል እያሟጠጠች አቅጣጫዋን ወደ ሰሜን አደረገች ።

ጥቂት እንዳዘገመች ደግሞ ቁስለኛው ተንፈራገጠ ። …



በዚያ ብርዳማ ሌሊት ላብ አሰመጣት ። የተሸከመችውን ወጣት ሞት የሚቀማት መሰላት ። ክፉኛ ሲንፈራገጥባት አወረደችውና መስኩ ላይ በጀርባው አሳረፈችው ።

ለመገነዣ የሚያገለግል አቡጀዲ ጨርቅ ከትጥቋ አወጣ ችና በሳንጃ እየተለተለች የቁስለኛውን ትከሻ በብብቱ እያዞረች አሰረችለት ።

ቁስለኛው ፀጥ ብሏል ። 'ውሃ !' አይልም ። አያቃስ ትም። አይንፈራገጥም ።

"ብርሃኑ !" አለችው ሁኔታው አስግቷት ።

ቁስለኛው ትንፋሽ አጥሮታል ። እንደምንም ብሎ በዚያ ድቅድቅ ጨለማ አይኖቹን ከፈተ ። የእሳት ጉማጆች እየተምዘገዘጉ እልም ሲሉ ታዩት ። የእሳት ጉማጆች ሲወረ ወሩ የሚያሰሙትንም አሸባሪ ድምፅ ሰማ ። ቦግ ! እልም ! … ሕይወት ! … ሞት ! ያ ነበር ቅፅበታዊ የጦር ሜዳ ትርኢት ።

ግራ እጁን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረገና "ማነሽ ?" አላት ።

"እንወይ ነኝ ! በርታ ባክህ ብርሃኑ !" ንግግሯ የልመና ቃላት ነበረው ።

"እንወይ !?" አለ ቁስለኛው ንግግሩን ረገጥ አድርጎ ። "ታዲያ እዚህ ምን ታደርጊያለሽ ? ምሽግሽን ለምን ትለቂያ ለሽ ? እቅድሽን እያፋለስሽ ነሽ'ኮ ! ሂጂና መትረየሴን ያዢው …" ንግግሩን ድንገት አቋረጠና አንቋረረ ። ወዲያው ደግሞ ጀመረ ። "መትረየሴን … መትረየሴን …"

እጇን ጥብቅ አድርጎ ይዟል ። ትንፋሹ ፈጣን ነው ። የልቡ ምትም እንደዚያው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ናረ ።

"ኧረ ዝም በል! የውጊያ ወረዳ ውስጥ'ኮ ነው ያለነው … " ወደ ጆሮው ተጠግታ አንሾካሾከችለት ። ያዳመጣት አይመስልም ።

"ልጄን … የዛሬ ወር ገደማ የሚመጣልኝን እንግዳ … ! ሳላየው ማለፌ ነው'ኮ! …አዲስ አበባ መቼ ነው የምን ገባው ? … ልጄ ስሙ ማን መሰለሽ ? ሴት ከሆነች …"

"አይዞህ ፡ ወንድማለም ! እንዲህ አታስብ ። … ስጋ ብዖት !" የመጨረሻዎቹ ሁለት ቃላት መሀላዋ ናቸው ። በህይወት እንደሚቆይ ያላትን ፅኑ እምነት የገለጠችባቸው ።

ግን አልሆነም ንግግሩን አቋረጠ ። ፀጥ አለ ። ትንፋሹ ጠፋ ። ከሰኮንድ በፊት ህያው ነበር ። ግኡዝ አካል ሆነ ። ቅፅበታዊ ለውጥ ! …

ደረቱ ላይ ተደፍታ ተንሰቀሰቀች ። እንባ ግን አልነበራትም ። ማዳን ትችል ይመስል እየተስረቀረቀችና ሳግ እየተናነቃት መላ አካሉ ላይ ጆሮዋን እየለጠፈች የሕይወት ምልክት ፈለገች ። ሞት የቀደማት መሆኑን ለማመን ጥቂት ጊዜ አጠፋች ። …

ሬሳውንም ቢሆን እዚያው ጥላ ላለመሄድ ወስና ካቀረቀረችበት ቀና ስትል አንድ ከቁመናው ዘለግ ያለ ሰው ፊቷ ላይ ተገትሯል ። አስተዋለችው ። ከላሸኗን ለማንሳት ጐንበስ ስትል በጠንካራ እጁ አፈፍ አድርጓት ፣ ፀጉሯን ጨምድዶ ያዘና ከአፎቱ የመዘዘውን አብረቅራቂ ሳንጃ ወደ ጉሮሮዋ አስጠጋው ። …

ንጋት ላይ የሸሚዛቸውን እጅጌ ወደ ላይ የሰቀሰቁና ጭናቸው ላይ ገመድ የጠመጠሙ ፣ ጠርብ ጠርብ የሚያክሉ



ወታደሮች ይጨፍራሉ ። እንወይ መካከላቸው አለች ።

"ይለያል ይለያል ይለያል
ይለያል ዘንድሮ
የወንበዴ ኑሮ !" … እያሉ ይዘላሉ ።

እጆቿ የኋሊት ተጠፍረዋል ። ደረቷ ላይ "ሻእቢያ !" የሚል ፅሁፍ የተፃፈበት ካርቶን አንጠልጥለውባታል ። እንወይን መካከላቸው ገትረው ዙሪያዋን እየዞሩ ይዘላሉ ። ይህ ሲበቃቸው ደግሞ እየነዱ ትና ጮቤ እየረገጡ ፣ "ይለያል … ይለያል …" እያሉ ወደ ሀይቅ ከተማ ይገሰግሳሉ ።

ከሀይቅ ከተማ ወጣ ብሎ ወደሚገኘው የጦር ግቢያቸው ሲቃረቡ ድምፃቸው በጣም ጐልቶ ይሰማ ጀመር ።

የጦር ግቢው በራፍ ሲደርሱ አንድ የሃምሳ አለቃ እጆቿ የኋሊት ተጠምዘው የታሰሩበትን ገመድ በግራ እጁ ይዞ ፣ በቀኝ እጁ የተቀባበለ ሽጉጡን ጭንቅላቷ ላይ እንደደገነ የግቢውን በር አልፎ ገባ ።

ወደ አንድ ቆርቆሮ በቆንቆሮ ወደተገጣጠመ ክፍል ወሰዳትና በሩን አንኳኩቶ ገባ ።

አንድ የመቶ አለቃ ማእረግ ያደረገ ራሰ በራ ወታደር አቀርቅሮ ይፅፋል ። ምናልባት የሚፅፈው ስለሌሊቱ ውጊያ ዝርዝር መግለጫ ይሆናል ።

"ጌታዬ ! የተማረከች ወንበዴ ናት !" አለ የሃምሳ አለቃው በተጠንቀቅ እንደቆመ ።

"ምን አስቀያሚዋ ናት ባካችሁ !?" አለና ምራቁን ጢቅ አደረገ ። ሰው አልመሰል አለችው ፣ ። ሻምበሉ "አስቀምጣት !" አለና በሃምሳ አለቃው ላይ ደነፋ ። የሃምሳ

አለቃው በፀጉሯ ጉትታትና ወንበር ላይ ዘጭ አደረጋት ።

በገመድ የኋሊት ተጠምዘው የተተበተቡት እጆቿ ይጠዘጥዟታል ። ድካም አዝለፍልፏታል ። ለአንድቀን ተኩል ያክል እረፍት ያጡት አይኖቿ ይቆጠቁጧታል ። ረሃብ ይሞረሙራታል ። አልፎ አልፎ ሆዷ ይጮሃል ። አንገቷን ሰብራ ፣ አይኖቿን ወለሉ ላይ ተክላ እንደተቀመጠች "ይለያል … የወያኔ የወንበዴ የሻእቢያ ኑሮ … ይለያል ዘንድሮ !" የሚል የበርካታ ሰዎች ድምፅ የጆሮዋን ታምቡር ሊበጥሰው ነው ።

"ሂድና አራት ኮማንዶዎች ፣ ሾፌሩንም ጥራ !" አለ ሻምበሉ ። ሃምሳ አለቃው በተጠንቀቅ እንደቆመ ደረቱን ነፋና ትእዛዙን ከተቀበለ በኋላ ወጣ ።

ሻምበሉ ሲጋራውን ሳብ አደረገና እፍፍፍ … አለባት ፣ በጥላቻ እየተመለከታት ። ዘላ የምትጎበርበት አውሬ መሰለችው ። በዚያች ክፍል ውስጥ ብቻውን ከሷ ጋር መቅረቱ ፍርሃት ፍርሃት አለው ። ሽጉጡን ከማህደሩ አወጣና አቀባብሎ ያዘ ።

"ጡት ነካሽ !" ከንፈሩን ነከሰባት ።

ትጥቃቸውን ያሳመሩ አራት ወታደሮች የሃምሳ አለቃውን ተከትለው ገቡ ፣ ታጣፊ ክላሽናቸውን እንዳነገቱ ።

"ነገውኑ በአስቸኳይ ደሴ ውሰዷትና ለሻምበል ክብረት አስረክቧት !" ብሏቸው ሽጉጡን ወደ ማህደሩ መለሰ ።

ይዘዋት ወጡ ። …

'ልዩ የምርመራ ክፍል' የሚል ፅሁፍ አናቷ ላይ የተለጠፈባትን ጠባብ ክፍል በር ከፈቱና ወደ ውስጥ



ገፈተሯት ። በሯ ከውጪ ተቆለፈች ።

በክፍሏ ውስጥ የታመቀው ግማት ገና ከርቀት አፍንጫ ይሰረስራል ። ጥግ በኩል የቆመው ጉርድ በርሜል በሽንት ጢም ብሏል ። ግድግዳዎቹ ተባይ ይርመሰመስባቸዋል ። በጣራውና በግድግዳው መጋጠሚያ ላይ መስኮት ተብየ አንዲት ክፍተት አለች ።

እንወይ ገና እንደገባች አጥወለወላት ። ቋቅ አላት ። ግን ከሆዷ የምታስወጣው ነገር አልነበራትም ። አፏንና አፍንጫዋን ለማፈን ሞከረች ። የማይቻል ነገር ሆነባት ። እንቅልፍ ስላንጎላጃት እንደምንም እየዳኸችና እየተንፏቀቀች ግድግዳውን ለመደገፍ ቻለች ። ጭንቅላቷን አንዴ ወደፊት ፣ አንዴ ወደ ግራ ፣ አንዴ ወደ ቀኝ እያዘነበለች ፣ እንቅልፍ ሸይበልው ሽልብ አደረጋት ።

በድንገት በሯ ብርግድ ብሎ ሲከፈት አይኖቿን ገለጠቻቸው ። አንድ ሰው ወደሷ ጠጋ አለና አንድ ትልቅ ጣሳ ውሃና ሁለት የደረቁ ዳቦዎች አስቀመጠላት ። ፀጉሯን ጨምድዶ በመጎተት ጥቂት አንፏቀቃትና የታሰረችበትን ገመድ ፈታላት ። ወዲያው እየተጣደፈ አፉንና አፍንጫውን አፍኖ ወጣ። በሩን ደርግሞባት ከውጪ ቆለፈው ።

በገመድ ተተብትበው የነበሩት እጆቿ አባብጠዋል ። አንዱን እጇን በአንዱ እየዳሰሰች ጥቂት ካስተዋለች በኋላ አስቀድማ የያዘችውን ጣሳ አነሳችው ። ወደ ደረቁት ከንፈሮቿ በቀላሉ ልታቀርበው አልቻለችም ። አብዛኛው በደረቷ ላይ ፈሰሰ ።

የቀረውን ውሃ ጭንቅላቷ ላይ ደፋችውና ጣሳውን ወደ

ጥግ ወረወረችው ። አንዱን ደረቅ ዳቦ አንስታ ተያያዘችው ። ብዙ እያጣጣረችና እያንቋረረች የግድ ጨረሰችው ።

በደረቷ ኂ ብላ ተደፍታ ማሰብ ጀመረች ። በዚያን ወቅት ወገኖቿ አንድ ላይ ተሰብስበው የውጊያውን ሂደት ሲገመግሙ ታዩዋት ። "እንወይ የት ቀረች?" የሚል ጥያቄ በድንገት ተነስቶ "ተሰውታለች !" በሚል ድምፅ ሲደመድሙ ታሰባት ። …

ያለችበት ግቢ ፀጥ ረጭ ብሏል ። አንዳችም ድምፅ አይሰማም ። ዙሪያውን ያሉ ተረኛ ዘቦች የብረት ቆባቸውን ደፍተው ፡ ክላሽናቸውን በረዥም ማንገቻ አንጠልጥለው ፡ አመልካች ጣቶቻቸውን ቃታቸው ላይ እንዳሳረፉ ይንጐራደዳሉ ። አልፎ አልፎ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ይሰማል ።

ሌሊት ዶሮ ሲጮህ ሻምበሉ ሁለት ወታደሮችን አስከትሎ የልዩ ቢሮውን በር ከፈተና ወንበሩን ያዘ ። ከፊት ለፊቱ አንድ መናኛ ጠረጴዛ ይገኛል ። ጠረጴዛው ላይ ደግሞ አንድ አኮርባጅና የተበታተኑ ወረቀቶች አሉ ። ክሯ አልቆ ባት የምትጨናበሰው ፋኖስ ጭል ጭል እያለች የደበዘዘ ብርሃን ትፈነጥቃለች ።

ሻምበሉ ፓኬት ሲጋራውንና ክብሪቱን ከኪሱ አውጥቶ ጠረጴዛው ላይ አደረገ ። በረዥሙ አፋሽገና እንቅልፍ ያልጠገቡ አይኖቹን እያጉረጠረጠባቸው "አምጧት !" አላቸው ፡ ወታደሮቹን ።

ሁለት እጆቿን የኋሊት ጠምዘው መደገፊያ የሌለው ወንበር ላይ አስቀመጧትና እነሱ ግድግዳውን ተደግፈው ቆሙ ።



ሻምበሉ ሲጋራውን ለኮሰና ብእር አንስቶ ፡

"ስምሽ ማነው ?" አላት

ዝም ።

"አማርኛ ትሰማለች ለመሆኑ ?" ወታደሮቹን ቀና ብሎ አያቸው ።

"እረ ጌታዬ ሻእቢያ ናት አሉ ! እነሱ ደግሞ አረብኛ ቢሆን ነው ቋንቋቸው …" ሲል ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር መለሰለት ።

"ስምሽን ንገሪን !" ሻምበሉ ለሶስተኛ ጊዜ ሞከረ ።

"እንወይ ?"

"እድሜሽ ?"

"ሃያ አራት !"

"አገርሽ የት ነው ?"

"ኢትዮጵያዊ አልመስልም ?" አለችው ስልል ባለ ድምፅ ።

"እሱን ተይው !" አለና ሻምበሉ ወታደሮቹን እያየ ፈገግ አለ ። ፈገግታው የለበጣ ነበር ።

"እሺ ያደግሽበት ?"

"ሰቆጣ !"

"ስራሽ ምንድነው ?" አፍጦ ተመለከታት ።

ዝም ።

"ስራሽ ምንድነው ?"

ጭጭ ።

"ግዴለም ! ገንጣይ ልንለው እንችላለን ! … "

"ተጋዳይ !" አለችው በእልህ እስትንፋስ ።

"ውይ ! ተጋድለሽ ሞተሻል !" አለና ሻምበሉ አፌዘ ባት ። ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር ፈገግ አለ ፤ ሻምበሉን ተከትሎ ።

"የሚቀጥለው ወረራችሁ በየት በኩል ነው?" ሲጋራ ውን ልምጥጥ አድርጐ ሳበና መተርኮሻው ላይ አወደማት ። መልሷን በጉጉት ይጠባበቃል ። ይቺን ጥያቄ በማስረጃ አስደግፋ ከመለሰችለትና ካስፈረማት የሚጠብቀው ሹመት ታየው ። በተለይም በዚህ ውጊያ በርካታዎቹ የተቀላጠፈ ማእረግ አግኝተው ፤ ወር ሳይሞላቸው አዳዲስ መረጃዎች በማጠናቀር ለአለቆቻቸው እያቀረቡ ለበለጠ ማእረግና ሽል ማት ሲበቁ እሱ አልቀናውም ። በዚህ ምክንያት አዲስ ነገር ለማግኘት ሲል የተመርማሪዎቹን የመመለስ አካላዊ ብቃት እንኳ ግምት ውስጥ ለማስገባት አይፈልግም ። ካልመሰላችሁ ልኝ ብሎ ደሙ ይፈላል ። በተለይም የተቃዋሚዎቹ የማጥ ቃት አቅጣጫ ባልተጠበቀ ጊዜና ባልተገመተ አካባቢ እየመጣ ፤ መንግሥት ሁኔታውን ለመቆጣጠር እንደተቸገረ ከመከላከያ ሚኒስቴር የተሰራጨው መግለጫ አሳሳቢ ሆኖበ ታል ። ስለዚህ ለማእረግና ለሹመት የመቋመጡን ያህል አንገቱንም እንዳይቆረጥ ይሰጋል ።

ተመርማሪዎቹ ውሸታቸውን ቢቀጹለትም ግድ አልነበ ረውም ። ብቻ የሚያስተላልፈው ነገር ይፈልጋል ። ታዲያ እንወይ የምትመልስለት አልሆነችም ።

"የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?" ጥያቄውን ደገመላት ፤ አኮርባጁን እየጠበጠበ ።

መልስ አልሰጠችውም ።



"ተናገሪ!"

ምንም ።

ወታደሮቹን በአይኑ ጠቀሳቸው ።

ረጅሙና ቦርጫሙ ወታደር በርጥበት የተኮማተረውን የሸሚዟን ክሳድ ጨምድዶ ወደ ላይ አነሳትና ፊቷን በቡጢ ለጋው ። ሲለቃት ወለሉ ላይ ድፍት አለች ። እንዳች በሚያካክሉት ጫማዎቹ የተዘረጉ ሁለት እጆቿን ጨፈላለቃ ቸው ። በጀርባዋ እንድትጋደም አደረጋትና ሆዷን ረገጣት ። ከተዘረጋችበት ወለል እንደገና አነሳትና በሁለትእጆቹ በጥፊ አጣደፋት ። ትንፋሽ ለማግኘት ቆም ሲል እሷ ዘጭ አለች ። የዝናብ ውሃ ከተጠራቀመበት በርሜል ባልዲ ሙሉ ቀድቶ ላይዋ ላይ ቸለሰባት። ውሉን ማወቅ በሚያስቸግር ዘዴ ሁለት እግሮቿን ተበተባቸው ። በሁለት እግሮቿ የውስጧ ክፍሎች ላይ ዘይት አፈሰሰባቸውና በጋለ ሽቦ ሲዳስሳቸው ተንፈራገ ጠች ። ክፉኛ ተወራጨች ። የጣእር ድምፅ አሰማች ።

ሻምበሉ ፈገግ እያለ ሌላ ሲጋራ ለኮሰ ። ሁለቱ ወታደሮች የወሳንሳ አንስተው ወንበር ላይ አስቀመጧት ።

ጭንቅላቷን ጠረጴዛው ላይ አስደገፈች ። ፊቷ ከመቅጽ በት ጥቅርሻ መሰለ ። የታሰሩት እጆቿ ብቻ ሳይሆኑ የጋለ ሽቦ የዳሰሳቸው እግሮቿም ጠዘጠዟት ። በልቧ ሞትን ተመኘች ። እሱም ቢሆን ሲፈልጉት ቶሎ የማይገኝ ሆነባትና የሞት ጥማት ያዛት ።

"ይህ በጣም ቀላሉ እርምጃችን ነው ፤ አይግረምሽ!" ሻምበሉ አሁንም አኮርባጁን ጠረጴዛው ላይ ይጠበጥባል ። "ይልቅ ፍጠኝ! የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?"

መልስ ባለማግኘቱ የተናደደው ሻምበል ከፓኬቱ ሌላ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰና የማገውን ጢስ ወደ አይኖቿ እፍፍፍ… እያለ "እሺ ይህ ይቆይልን! በየትኛው ድርጅት ውስጥ ነበርሽ? አላት ።

"ኢህዴን!" አለችው ወኔ በሳለው አንደበት ።

"ከመቼ ጀምረሽ ወንበዴ ሆንሽ?"

"ወንበዴ አይደለሁም! ታጋይ ነኝ ። ወደ ትግል መስክ የገባሁትም በ82 ዓመተ ምህረት ነው ። የዋለለኝ ሬጂመንት አባል ነኝ!"

"የዋለለኝም በይው የሳዳም ሁሴን ፣ የንጉስ ፋአድም ይሁን የአንዋር ሳዳት ሬጅመንት ፣ ቡድናችሁ ያው ዞሮ ዞሮ ወያኔ ሻእቢያ ማለት አይደለም?"

"አይደለም!" ቀሪው አቅሟን መልስ ልትሰጥበት ቆርጣለች ።

"የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?" የጉሪጥ ተመለከታት።

"አላውቅም!"

"ለምን አታውቂም?"

"አላውቅም!"

ሻምበሉ ከመቀመጫው ብድግ አለና በያዘው አኮርባጅ ጀርባዋን ተለተላት ፣ ክንዱ እስኪዝል ድረስ ።…

"አትናገሪም?" በላብ የተጥለቀለቀውን ግንባሩን እየጠረገ ።

"ባልናገርስ!?" አይኖቿ እምባ አቅረዋል ።

"ባትናገሪማ ውሃ የሞላ በርሜል ውስጥ እንዘፍቅሽ



ለን። ከዚያ አውጥተን ደግሞ በአፍሽ የገማ ካልሲ ጎርሰሽ በዚህ አለንጋ ፍዳሽን ትቆጥሪያለሽ ፤ ወያኔ ውስጥ የገባሽበትን እለት እስክትረግሚ ድረስ!"

"ከዚያስ!?"

"ከዚያ በኋላማ በስለታም ሳንጃ ይህ ገንጣይና አስገንጣይ ምላስሽ ይቆረጥና አንድ አይንሽ ተወግቶ ይፈስሳል ። ቀጥሎም እጆችሽ የኋሊት ተጠምዘው ሕዝብ ተሰብስቦ 'ወያኔ ሌባ! ወያኔ ገንጣይ!' እያለ እያጨበጨበብሽ ከተማውን ስትዞሪ ውለሽ ፣ በዛገ ምላጭ ይህን ቅጫማም ጉፈሬሽን ተላጭተሽ መቀመቅ ትወርጃለሽ!"

"አዲስ ነገር አልሰማሁም ። አድራጎታችሁ ይኸው እንደሆነም አላጣሁትም ። ማሳረጊያችሁ ዞሮ ዞሮ ያው ሞት ነው ፣ አይደል?"

አስፈሪ ዛቻው በአእምሮዋ እንዲቀረጽና ከዚያ ለመዳን እንድትዘጋጅ ለማድረግ ሻምበሉ ሌላ ነገር ሳይጨምር ክብሪቱንና ፓኬት ሲጋራውን ይዞ ወጣ ።

ቀጭኑና አጭሩ ወታደር እንደተደበተ ወደ መኝታው ሄደ ። ረዥሙና ቦርጫሙ ወታደር ሻምበሉን ተከትሎ ወጥቶ መኝታ ክፍሉ ድረስ ካጀበው በኋላ ፣ ሻምበሉ ገብቶ መብራቱን አጠፋ ። ቦርጫሙ ወታደርም ወደ ተመርማሪዋ ክፍል ተመለሰ ።

ፋኖዷ ጭል ጭል እያለች የተጨናበሰ ብርሃን መስጠቷን አላቆመችም ። ወደ እንወይ ተጠጋ ። ጉትቶ አስቆማት ። ለአንድ ሳምንት ያክል ከገላዋ ተጣብቆ ያልተለያትን ፣ በጭቃና በዝናብ የላሸቀ ሱሪዋን ማውለቅ ጀመረ ። ያባበጡት

እጆቿ ፈርጣማ ክንዶቹን መቋቋም እንደማይችሉ አውቋል ። ያስቸገረው ከሰውነቷ ጋር የተጣበቀው ሱሪዋ ነበርና ሳንጃውን ከአፎቱ መዝዞ ከላይ ጠርዙ እስከ ጉልበቷ ድረስ ተረተረው ። ሳንጃውን ወደ ቦታው መልሶ የራሱን ሱሪ ዝቅ አደረገ ። ባለ በሌላ ኃይሏ ተከላከለችው ። አልቻለችም ። ለመጮህ አፏን ከፈተች ። በአንድ እጁ ጥርቅም አድርጐ አፈነባት ። ስልምልም አለችበት ። የሞተች መስሎት ለቀቃት ። ትውከቷን ወለሉ ላይ ለቀቀችው ። ሀሞት ደፈቃት። …ጓጉራት ። ያልተሳካለት ቦርጫሙ ወታደር ሱሪውን እየታጠቀ ወጣ ።

ይህን ዘግናኝ አድራጐቱን በስርቆሽ ሲታዘብ የቆየው አጭሩና ቀጭኑ ወታደር በሳንጃው ተቀበለው ። ሬሳውን ጐትቶ አሳቻ ቦታ ወተፈና ጠባቂ መስሎ እንወይ በር ላይ አደፈጠ ።

እኩለ ሌሊት ላይ ምሬትና ብሶት እያንሰፈሰፋት ስብርብር ባለና በደከመ ድምፅ እንወይ ማዜም ጀመረች ፤ ትንፋሿ ተመልሶላት በሕይወት መኖሯን ስትገነዘብ ።

“የትላንቱን አልፈን — ዛሬም እንደገና ሌላ ቢከተለን
እንደ ልማዳችን — ንፁሕ ደም ገብረን እንወጣዋለን!
ችግርና ቀውጢ ወትሮም አንድ ላይ ነው
ቀውጢን አልፎ መቆም የታጋይ ፀጋ ነው!…”

ሌላ ዜማ ደግሞ ጀመረች ፤ በረሀ ውስጥ በምትማስንበት ወቅት የምትደጋግማቸውን ስንኞች እየደረደረች ።

“የከፋ የከረፋ—መአት ይውረድብን ፤
ልክ የለሽ መከራ—እንቅፋት ይግጠመን ፤



ዩፋሽስቶች ነዲድ—ነበልባል ይግረፈን ፤
ክልሱ እምነታቸው—ውሽት ያናፋብን ፤
በትግል በእምቢታ—በአመፅ እንጠራለን!…”

አስራ አንድ ሰአት ላይ ሻምበሉ አጭሩንና ቀጭኑን ወታደር አልፎ በሯን በርግዶ ገባ ። “ሻእቢያ ያስማገሽ ሀቪ የሚጭርልሽ የእብሪት ስሜት ገና አልበረደልሽም?” አላት ። ጥርሶቹን ነክሶባት በንዴት እየተርገፈገፈ ።

“የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?” ንዝንዙን ቀጠለ ። ጭንቅላቱ ግሏል ። ፊቱ ተኮሳትሯል ። ጣቶቹን ይጨብጣል ፤ ይዘረጋል ። አይኖቹ ግሽርጥ መስለዋል ።

“ትናገሪያለሽ አትናገሪም?”

“ምን ልናገር?” አለችው የሞት ሞቷን ።

“የሚቀጥለው ወረራ በየት በኩል ነው?”

“አላውቅም!”

“አትናገሪም?”

“ምን ብየ?”

“ተናገሪ!”

“እናቸንፋለን!” አለችው ግራ ክንዷን ሽቅብ እየወረ ረች ። ጭኑ ላይ አንጠልጥሎት የነበረውን ሳንጃ ከአፎቱ መዘዘና አንገቷ ላይ ሰካው ። መዘዘና ግራ ጡቷ ላይ … ሽንጧ ላይ … በደም አበላ የተነከረውን ሳንጃ ከግራ ሽንጧ መሐል እናቷ ላይ ተከለው ።…

አካባቢው ጭር እንዳለ ነው ። ሌሊቱ የሚጨል ሊነጋጋ ሲል ነው እንዲሉ ድቅድቁ ጨለማ የበለጠ ከብዷል ። ከርቀት የጥይት ድምፅ ይሰማል ።

ሻምበሉ ያላበውን ማጅራቱንና ግንባሩን በመሀረብ እየጠራረገ በጉራ ተሞልቶ በመንጐራደድ ላይ ሳለ ሳያስበው ሳንጃ ከነእጀታው ከበስተጀርባው ተቀበቀበበትና ባፍጢሙ ተደፍቶ ፀጥ አለ ።

ተጭኑና አጭሩ ወታደር ከአንጀቱ የሚገነፍልበት ሀቃቃውን ለማፈን ቢታገልም ጉንፋጮቹ በእንባው ራሱ ። ጭል ጭል የምትለዋ ፋኖስ በምትሰጠው የደበዘዘ ብርሃን በደም የጨቀየውን ወለልና በጀርባዋ የተንጋለለችውን ወጣት አየ ። በእልህ ሲቃ ተቅበጠበጠ ።

ለመጨረሻ ግዜ ትክ ብሎ ተመለከታትና መሳሪያውን እንዳነገተ ከግቢው ወጣ ። አልተመለሰም ። ፀጉሩን አንጨፍሮ ፥ ኮንጐ ጫማ አጥልቆና ፥ ሽጉጥ ታጥቆ ፥ ከ“ሚያዝያው የዋለለኝ ማእበልተኞች” ጋር ሰልፉን አስተካክሎ ደሴ ላይ ብቅ እስካለበት ጊዜ ድረስ የት እንደገባ የገመተ ማንም አልነበረም ።

ከ73 — 83 ዓ.ም.
‘ለቀውጢ ቀን ኮከብ!’

ሞት ይርሳኝና ዘንግቻት የነበረውን የእድሜ ድባቤን ፣ የህይወት ርካቤን ፣ ያቺን ጐስቋላ ዛኒጋባየን ነው ‘ሰውና ሰው’ ያስታወሰችኝ ። የኑሮን ዝብርቅርቅ ፣ የአልሞት ባይተጋዳይን ትንቅንቅ አሳየችኝ ። ‘ሰውና ሰው’ ነፍሴን በትዝታ አንጥራ… የነገ እይታየንም አጥርታ ፅንቶ መቅናትን ያስተማረችኝ ውብ ፅሁፍ ናት ።

ወጣቱ ደራሲ ፀሀዬ መሰለ እደግ – ተመንደግ የሚያሰኝ ስራ አበርክቷል ። ማንም አንባቢ “ሰውና ሰው”ን በደምብ ያጣጥማታል… ይማርባታል ።

ሚሲግ ሚካኤል

ዋጋው ብር 5·75

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ